ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 326 ሐምሌ 26 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# "እንደ ሀገር ያጣነውን ነገር ለመጠገን የኃይማኖት አስተምህሮ አስፈላጊ ነው"

- ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ



አዲስ አበባ፡- እንደ ሀገር ያጣነውን ነገር ለመጠገን የተባበረ ክንድ እና የኃይማኖት አስተምህሮ አስፈላጊ በመሆኑ ጉባዔው ትኩረት ሊያደርግበት ይገባል ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ገለፁ።

ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ የኢትዮጵያ ኃይማኖት ተቋማት ጉባዔ 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔና የእውቅና መድረክ ትናንትና ሲካሄድ እንደገለጹት፤ የሀገርን ሰላም ለማስጠበቅ ያለብንን ኃላፊነት ልንወጣ ይገባል። እንደ ሀገር ያጣነውን ነገር ለመጠገን የተባበረ ክንድ እና የኃይማኖት አስተምህሮ አስፈላጊ በመሆኑ ጉባዔው ትኩረት ሊያደርግበት ይገባል።

በኃይማኖቶች መካከል የአብሮነት እሴትን ሊያጠናክሩ በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንደሚገባ ገልጸው፤ የኃይማኖት ተቋማት ለሀገራዊ የሠላም ግንባታ ከፍተኛ ሚና አላቸው። በኃይማኖቶች መካከል የአብሮነት እሴትን ሊሸረሽሩ የሚችሉት ጉዳዮችን መከላከል ከኃይማኖት ተቋማት ከፍተኛ ስራ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንት ሳህለ ወርቅ፣ የኃይማኖት አባቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ተሰሚነት ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፤ ይህን ተሰሚነታቸውን ተጠቅመው ምዕመናንን ስለ ሰላምና አንድነት በማስተማር ሀገራዊ ወሳኝ ጊዜያትን ለማለፍ የላቀ ሚና መጫወታቸውንም አንስተዋል።

ለሀገራችን ዘላቂ ሰላምና አንድነት የኃይማኖት አባቶች መንፈሳዊ ድጋፍና የተባበረ ክንድ ያስፈልጋልም ብለዋል።

የኃይማኖት ተቋማት ልዕልና እና ክብር ተጠብቆ እንዲቆይ ሁል ጊዜም ጥረት እንደሚፈልግም አስገንዝበዋል።

የሠላም ሚኒስትር ዴኤታ ኸይረደን ተዘራ (ዶ/ር)

"እንደ ሀገር ያጣነውን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከቅጣት በፊት
## ለሕግ መገዛት ለምን ተሳነን?

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ሕግና ሥርዓትን በማበጀት ረገድ ሀገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ እንዳላት መዛግብት ያስረዳሉ:: ሀገሪቱን የመሩ ሥርዓተ መንግሥታት እንደየዘመናቸው የየራሳቸው መተዳደሪያ ሕግ ነበራቸው:: ሕዝቡም አምላኩን የሚፈራ ለህገኑም ሕግ የተገዛ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ::

አባቶቻችን የሚታወቁበት የማኅበረሰብን ወግና ደንብ አክባሪነት፤ መንግሥታት ላወጡት ሕግ ተገዢነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ መጥቷል:: ለዚህም በየጊዜው የምንሰማቸው ወንጀሎች፣ እያወቅን የምንጥሳቸው በርካታ ደንቦች ምስክሮች ናቸው::

የትራፊክ ሕግን እንዲከበር፣ ጤናማ የንግድ ሥርዓት እንዲፈጠር፣ አካባቢን ብሎም ከተሞችን ከቆሻሻ የጸዱ ለማድረግ፣ የራሳችን ሀብት የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ከጉዳት ለመታደግ ሕግ ማውጣቱ ብቻ በቂ አልሆነም:: እንደ ማኅበረሰብ ሕግ ቢከበር ጥቅሙ ለእኔው የሚል አመለካከት ብዙም ሰርጾ አይታይም::

ሕግ ለማክበር በመጠኑም ቢሆን የምንነሳው ሕግ የማስከበሩ ሥራ ወደ ቅጣት ሥርዓት ሲገባ እንደሆነ የሕግ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: ሰዎች አንድ ድርጊት በሕግ ያስጠይቃል ወይ ከማለት ይልቅ ሕግ አስከባሪ አይቶናል ወይ ለሚለው ትኩረት የሚሰጡ

ከቅጣት በፊት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በገበያ የሚወሰነው
## የውጭ ምንዛሪ ግብይት ቀጣይ የቤት ሥራዎች

ፋንታነሽ ክንዴ

መንግሥት ከሰሞኑ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ይፋ አድርጓል:: ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በደንበኞቻቸው

በገበያ የሚወሰነው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# "የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጡን በቁንጽል ሳይሆን በምልዐት መመልከት ይገባል"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጡን በቁንጽል ሳይሆን በምልዐት መመልከት ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የነበራቸውን መድረክ አስመልክቶ ትናንት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ እንዳሰፈሩት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጡን በቁንጽል ሳይሆን በምልዐት መመልከት ይገባል። በመደመር ዕሳቤያችን ለሀገር ልማት

"የማክሮ ኢኮኖሚ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የክልሉ ምክር ቤት የሕዝብን የልማት ጥያቄዎችና

## የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በሚቀርፉ ጉዳዮች ላይ ተወያይቷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የአማራ ክልል ምክር ቤት የሕዝብን የልማት ጥያቄዎችና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በሚቀርፉ ጉዳዮች ላይ መወያየቱን አፈ ጉባዔ ፋንቱ ተስፋዬ ገለጹ።

የአማራ ክልል ምክር ቤት 6ኛ ዙር፣ 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 8ኛ መደበኛ ጉባዔውን የተለያዩ ውሳኔዎችንና ሹመቶችን በማጽደቅ ተጠናቋል።

የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ፋንቱ ተስፋዬ እንደገለጹት፤ የክልሉ ምክር ቤት የሕዝብን የልማት ጥያቄዎችና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በሚቀርፉ ጉዳዮች ላይ ተወያይቷል።

ምክር ቤቱ በመደበኛ ጉባዔው የክልሉን ወቅታዊ የሰላም፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን በስፋት ተመልክቷል ያሉት አፈ ጉባዔዋ፤ ምክር ቤቱ በመደበኛ ጉባዔው በተለያዩ ክልላዊ ጉዳዮች ዙሪያ ገንቢ ምክክሮችን አካሂዶ የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳርፏል ብለዋል።

ክልሉ ለአንድ ዓመት ከዘለቀው ግጭት ወጥቶ አንጻራዊ ሰላም በበርካታ አካባቢዎች መስፈኑን ጠቅሰው፤ የተጀመሩ የሰላም ጥረቶች ዳር እንዲደርሱ የሚያስችሉ ምክክሮች መካሄዱን ገልጸዋል።

በክልሉ ሕዝብን ያማረሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ በተለይም የፍትሕ ሥርዓቱን በሕዝብ



አፈ ጉባዔ ፋንቱ ተስፋዬ

ዘንድ ተዓማኒ ለማድረግ ምክር ቤቱ ምክክሮችን እንዳደረገ በመግለጽ፤ በየደረጃው የሚገኘው የምክር ቤት አባል ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንደሚኖርበትም መግባባት ላይ መደረሱን አስረድተዋል።

የሕዝቡን የመልማት ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በጀትን በቁጥጥርና በቁጠባ መጠቀም፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በየደረጃው ለመፍታት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ መወያየታቸውን አብራርተዋል።

በምክር ቤቱ የሕዝብን ጥያቄ እያዳመጡ በየደረጃው ምላሽ መስጠትን ጨምሮ የምክር ቤቱን የክትትልና ቁጥጥር አቅም ማጠናከር የሚሉ ጉዳዮች መነሳታቸውንም ጠቁመዋል።

ምክር ቤቱ በመደበኛ ጉባዔው የተለያዩ ደንቦችንና መመሪያዎችን መርምሮ ማጽደቁን የገለጹት አፈ ጉባዔ ፋንቱ፤ የክልሉን መንግሥት የ2017 በጀት መርምሮ አጽድቋልም ብለዋል።

በተጨማሪም በጀታቸው በምክር ቤት የሚጸድቅላቸው የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ምክር ቤትና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዓመታዊ በጀት ማጽደቁንም ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በምክር ቤቱ የክልሉን መንግሥት የ2017 በጀት 150 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ተወያይቶ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

ምክር ቤቱ የቀረቡለት ሹመቶችንም አስመልክተው አቶ ዓለምአንተ አግደው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ሙሉዓለም ቢያዝን ዓለሙ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፣ አቶ መልካሙ ፀጋየ ገላው የባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ እንዲሆኑ ማጽደቁን ተናግረዋል።

በተጨማሪም በክልሉ ምክር ቤት የቋሚ ኮሚቴ አባላት ለምክር ቤቱ ቀርቦ የጸደቀ ሲሆን፤ አቶ አበራ ፋንታው የሰው ሀብት አስተዳደር እና ቱሪዝም ልማት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እንዲሁም እመቤት ከበደ የመንግሥት ወጪ ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነው መሾማቸውን ማወቅ ተችሏል።



አቶ ሮት ጋትዌች

# በክልሉ በተከሰተ

## የዓይን በሽታ ወረርሽን በአራት ሳምታት ውስጥ ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች ተይዘዋል

**ማህሌት ብዙነህ**

ጋምቤላ፡- በጋምቤላ ክልል በተከሰተ የዓይን በሽታ ወረርሽኝ በአራት ሳምታት ውስጥ ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች መያዛቸውን የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ጤና ቢሮ ኃላፊ አቶ ሮት ጋትዌች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የዓይን ወረርሽኙ ከሐምሌ መጀመሪያ ጀምሮ በክልሉ ናሬ ወረዳ የተከሰተ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በሽታው ጋምቤላ ከተማን ጨምሮ በሁሉም የክልሉ ወረዳዎች ተከስቷል።

እስካሁንም ከአንድ ሺህ 300 በላይ ሰዎች በበሽታው የተያዙ መሆኑን አስታውቀው፤ ይህ መረጃም በመንግሥት ሆስፒታሎች የተገኘ ሪፖርት እንጂ በግል ህክምና ጣቢያ ወይም በቤት ውስጥ ህክምና የተሰጡትን የማያካትት መሆኑን ገልፀዋል።

በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለው ወረርሽኝ መሰል በሽታ በዓይን በማይታዩ ቫይረስ ወይም ባክቴሪያ በሚባሉ ተዋሕሲያን የሚከሰት በሽታ ሊሆን የሚችል መሆኑን ገምተው፤ የበሽታውን ምንነት ለማጣራትም ናሙና በመሰብሰብ ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

የዓይን መቅላት፣ የሚቆጠቁጥ የዓይን ሕመም፣ የዕይታ መቀነስ፣ የዓይን እብጠት፣ የማያቋርጥ ፈሳሽ ወይም ዕንባ እንዲሁም የዓይን አር መኖር የበሽታው ዋና ምልክቶች ናቸው ሲሉ አስረድተዋል።

በበሽታው የቀጥታ እጅ ንክኪ፣ ከተያዘ ሰው በሚወጡ የዓይን ፈሳሾች የተነካኩ ጨርቃ ጨርቅና መነፀር እንዲሁም የጋራ የውሃ ባኞ ቤቶች መጠቀም ዋነኛ የመተላለፊያ መንገዶቹ መሆኑም አስረድተዋል።

በመሆኑም እጅን ከዓይንም ሆነ ከቀጥታ ንክኪ መታቀብ፣ በበሽታው የተያዘ ሰው ሲጠቀምባቸው የነበሩ ቁሳቁሶችን አለመጠቀምም በወረርሽኙ ላለመያዝ መደረግ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪ በየጊዜው የእጅ ንጽህናን በውሃና ሳሙና፣ በአልኮል ወይም ሳኒታይዘር በተገቢው በመጠበቅ በሽታውን አስቀድሞ መከላከል የሚቻል መሆኑን ገልፀዋል።

እንዲሁም በበሽታው የተያዘ ሰው በአቅራቢያ ወደ ጤና ተቋም በመገኘት ሕክምና ማግኘት ጀምሮ በተቻለ መጠን የዓይንና እጅ ንክክኪ አለማድረግ፣ የግል እቃዎች ለይቶ መጠቀም እንዲሁም የዓይን መነጽር መጠቀም እንዳለባቸው ኃላፊው ተናግረዋል።

በሽታው በከፍተኛ ፍጥነት ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም የአካባቢ ንጽህና በተጓደለባቸው እና በርካታ ቁጥር ነዋሪዎች ያሉባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለበሽታው የመጋለጥ ዕድላቸው ሰፊ መሆኑን አስታውቀዋል።

የክልሉ ጤና ቢሮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለበሽታው ግንዛቤ የመስጠት ብሎም የቅኝትና ምላሽ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን አቶ ሮት ገልፀዋል።

ይህ በወረርሽኝ መልክ የተከሰተው የዓይን በሽታ ከፍተኛ የመተላለፍ ዕድል ያለው በመሆኑ ህብረተሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ ኃላፊው አሳስበዋል።

# ክረምትና የተማሪዎች አክራሞት

**ነፃነት አለሙ እና ቃልኪዳን አሳዬ**

ተማሪዎች ፈተና ጨርሰው ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል። ክረምት ልጆች የእረፍት ጊዜያቸውን በቤታቸው አለያም ወደሌላ አካባቢዎች በመሄድ ከዘመድ አዝማድ ጋር፣ ከሚወዷቸው ጓደኞቻቸው እና የዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር የሚያሳልፉበት ወቅት ነው።

ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለእረፍት ወደ ቤተሰቦቻቸው የሚሄዱ ወጣቶችም የበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ በመሳተፍ ለአካባቢያቸው ብሎም ለሀገራቸው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበት ጊዜ ነው።

በእውቀት የዳበረና በሥነልቦናው የጠነከረ ትውልድ መፍጠር ለነገ የማይባል ነው። ለዚህም ወላጆች፣ መምህራንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የየራሳቸው ሚና አላቸው። በተለይም በክረምት ወቅት ተማሪዎች ከመደበኛው የትምህር ገበታ ስለሚርቁ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው እደሚገባ የልጆች ሥነልቦና ባለሙያዎች ይመከራሉ።

ለመሆኑ ተማሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን ፍሬያማ በሆነ መንገድ እንዲያሳልፉ ወላጆችና አሳዳጊዎች እንዴት ሊደግፏቸው ይገባል?

በአዲስ አበባ ከተማ የፊት አውራሪ አባይነህ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ደረጀ ቶላ እንደሚናገሩት፤ ተማሪዎች በክረምቱ የሚኖራቸውን የእረፍት ጊዜ የፈጠራ ክህሎቶቻቸውን ማሳደግ በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ እንዲያሳልፉ ወላጆች ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

ተማሪዎች ክረምቱን በቴክኖሎጂ፣ በኪነጥበብ፣ በስፖርትና በሌሎችም ዘርፎች እንደየ እድሜያቸውና ፍላጎቶቻቸው እንዲሳተፉ በማድረግ ችሎታቸውን እዲያዳብሩ መርዳት ጠቃሚ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ተማሪዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደሥራው ዓለም በሚገቡበት ወቅት የራሳቸውን ውስጣዊ ክህሎት በመጠቀም ሥራ በመፍጠር ሀገራቸውን ማገልገል የሚችሉበት አጋጣሚ እንዲፈጠር እንደሚያግዛቸው ይገልጻሉ።

እንደ መምህር ደረጀ ገለጻ፤ ከሁለንተናዊ እድገት ጋር ተያይዞ ተማሪዎች እንዴት በራሳቸው መተማመንና ራሳቸውን ማሳደግ እንዳለባቸው፤ ክህሎቶቻቸውን አውጥጠው መጠቀም ስለሚችሉበት ሁኔታ እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ተግባቦት ምን መምሰል እንዳለበት ሥልጠናዎችን ቢወስዱ በብዙ ያተርፋሉ።

በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚዘዋወሩ ይዘቶች ታዳጊዎች ለአቻ ግፊት እንዲዳረጉ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን አንስተው፤ ይዘቶቹ ተማሪዎች



ራሳቸውን ከሌሎች ጋር እንዲያወዳድሩና ያዩትን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ እንዲነሳሱ ያደርጋሉ ይላሉ።

ስለዚህ ከማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ በተማሪዎች ላይ ክፍተት እየታየ በመሆኑ ወላጆች በአግባቡ እንዲጠቀሙ አቅጣጫ ማሳየት መቻል አለባቸው ሲሉም ይመክራሉ።

ተማሪ ሳሮን ቸርነት በደጃዝማች ባልቻ አባነብሶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ናት።

የክረምት ወቅት ተማሪዎች በቤታቸው የሚያሳልፉበት ጊዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጊዜያቸውን ሳያባክኑ ቤተሰቦቻቸውን በመርዳት፣ ስለሀገራቸው ታሪክ በማንበብና የክረምት ትምህርት በመማር ማሳለፍ እንደሚኖርባቸው ትናገራለች።

እንደ ተማሪ ሳሮን ገለጻ፤ ተማሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን በአግባቡ ማሳለፋቸው ለአዲሱ የትምህርት ዘመን ያላቸው ዝግጁነት የተሻለ እንዲሆን ያግዛቸዋል። እንዲሁም በየትኛው ሰዓታቸው ማንበብ፣ መጫወትና ከጓደኞቻቸው ጋር ጊዜ ማሳለፍ እንደሚችሉ ለይቶ በማወቅ ጊዜያቸውን በእቅድ መጠቀምን እንዲለምዱም ያደርጋቸዋል።

ታዳጊዎች የቤተሰብ፣ የመምህራን አለፍ ሲልም የሀገር ኃላፊነት እንዳለባቸው የምትገልጸው ተማሪ ሳሮን፤ ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ሰፊውን የእረፍት ጊዜያቸውን ቤት በሚያሳልፉበት ወቅት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ወላጆቻቸውን በማክበርና ምክራቸውን በመቀበል ራሳቸውን ለማሳደግ ጠንክረው መሥራት እንደሚገባቸው ትገልጻለች።

አቶ መንግሥቴ አራጋው የተማሪ ልዑል መንግሥቴ ወላጅ አባት ናቸው። ልጃቸው ልዑል የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን ከትምህርቱ ጎን ለጎን ከመኖሪያ ቤታቸው ፊት ለፊት ባለ ሜዳ ላይ እግር ኳስ መጫወትን ያዘወትራል። አሁን ላይም በታዳጊ ፕሮጀክት ታቅፎ እዚሁ ሜዳ ላይ ልምምድ እያደረገ እንደሚገኝ ወላጅ አባቱ ይገልጻሉ።

የክረምት ጊዜውን አልባሌ ቦታ ከማሳለፍ ይልቅ በማንበብና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በመሥራት በአካሉና በሥነ ልቦናው መጠንከሩ ለነገ ሕይወቱ እጅጉን ጠቃሚ መሆኑን የሚያነሱት አቶ መንግሥቴ፤ ልጃቸው ያለውን ክህሎት እንዲያዳብር የሚፈልገውን ማንኛውንም አይነት ነገር በማሟላት ድጋፍ እያደረጉለት እንደሚገኙ ይናገራሉ።

ልጆች የኪነጥበብ፣ የስፖርት፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራና ሌሎችም የተለያዩ ክህሎቶች ያሏቸው በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ቀርበው በማነጋገርና ፍላጎታቸውን በመረዳት በጎ ክህሎቶቻቸውን እንዲያዳብሩ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው ሲሉ መልዕክት ያስተላልፋሉ።


# ሕገወጥ ተግባራትን በሚፈጽሙ ነጋዴዎች ላይ ንግድ ፍቃድ እስከመሰረዝ የሚደርስ ርምጃ ይወሰዳል

## -71 ንግድ ድርጅቶች ላይ ርምጃ ተወስዷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ሰበብ በማድረግ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉና ምርት በሚደብቁ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ ንግድ ፍቃድ እስከመሰረዝ የሚደርስ ርምጃ እንደሚወሰድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቢሮው የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ይፋ ያደረገውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትሎ በመዲናዋ አንዳንድ ነጋዴዎች አላግባብ ዋጋ ጭማሪዎችን የማድረግና ምርት የመደበቅ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡




ቢሮው ይህን ሕገወጥ ተግባር ለመከላከል የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ሰውነት፤ በዚህ ድርጊት ተሳትፈው በሚገኙ ነጋዴዎች ላይም የንግድ ፈቃድ እስከመሰረዝ የሚደርስ ርምጃ ይወሰዳል ብለዋል፡፡

ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጊዜ ቢሮው ባከናወነው የክትትልና ቁጥጥር ሥራ 71 የንግድ ድርጅቶች ላይ ርምጃ መወሰዱን ያስታወቁት አቶ ሰውነት፤ ርምጃው ምርት በማከማቸት፣ በማሸሽ እንዲሁም ከ25 በመቶ በላይ አላግባብ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ የተወሰደ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የክትትልና ቁጥጥር ሥራው በቀጣይነትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ በሕገወጥ ሥራዎች ላይ በሚሳተፉ ነጋዴዎች ላይ ንግድ ፍቃድ እስከመንጠቅ የሚደርስ ርምጃ ይወሰዳል ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡፡

ቢሮው ከዚህ ቀደም ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን የመከታተልና መቆጣጠር ሥራዎችን እንደሚሠራ አስታውሰው፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ይፋ መሆንን ተከትሎ ከማዕከል እስከወረዳ ያሉ ባለሙያዎችን አሰማርቶ የበር ለበር ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ምርት የሚከማችባቸው ተብለው በተለዩ መጋዘኖች ላይም ፍተሻ እየተደረገ እንደሚገኝ ነው የተናገሩት፡፡

ቢሮው የሚያከናውነው ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ የህብረተሰቡ ጥቆማ ሕገወጥነትን ለመከላል ወሳኝ ሚና እንዳለው የገለጹት አቶ ሰውነት፤ ሕገወጥ ተግባትራን በመፈጸም ህብረተሰቡ ላይ ጫና የሚያደርሱና ማሻሻያው እንዳይሳካም እንቅፋት የሚፈጥሩ አካላት ላይ የሚያደርገውን ጥቆማ አጠናክሮ በመቀጠል ርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከ400 ሺህ በላይ ነጋዴዎች መኖራቸውን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ አብዛኛው ነጋዴ ሕግን አክብሮ ሥራውን እያከናወነ የሚገኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ ሕጋዊ ነጋዴዎች አላግባብ የዋጋ ጭማሪ በማድረግና ምርት በመደበቅ የንግድ ሥርዓቱን የሚረብሹ ነጋዴዎችን በመጠቆም ርምጃ እንዲወሰድባቸው ለማድረግ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

ማህበረሰቡ ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ሲመለከት በ8588 ነጻ የስልክ መስመር በመደወል፣ በየወረዳው ለሚገኙ የንግድ መዋቅሮች እንዲሁም በአቅራቢያው ለሚያገኛቸው የሕግ አስከባሪ አካላት ጥቆማውን ማድረስ እንደሚችል አቶ ሰውነት ጨምረው ገልጸዋል፡፡



ፎቶ ሃዲሽ አብርሃ

ከበደ ጋኖሌ (ኢንጅነር)

# በክልሉ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 360 ሺህ ዜጎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሶሎሞን በየነ**

ሃዋሳ፡- በክልሉ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 360 ሺህ ሕዝብ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የሲዳማ ክልል ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ። የክልሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ሽፋን 60 በመቶ መድረሱም ተነግሯል፡፡

የሲዳማ ክልል ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ ከበደ ጋኖሌ (ኢንጅነር) እንደገለጹት፤ በክልሉ በተጠናቀቀው 2016 በጀት ዓመት ብቻ 360 ሺህ ሕዝብ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ሲዳማ ክልል እንደክልል ሲቋቋም ንጹህ የመጠጥ ውሃ ሽፋኑ 38 ነጥብ 2 በመቶ እንደነበር የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ ክልሉ እንደ ክልል ከተቋቋመ ወዲህ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ሽፋኑን በእጥፍ ማሳደግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በዚህም ዘንድሮን ጨምሮ በአራት ዓመታት ውስጥ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ሽፋኑን ከ38 ነጥብ 2 በመቶ ወደ 60 በመቶ አድጓል ብለዋል።

ከክልልነት በኋላ በተፈጠረው ምቹ አስተዳደራዊ መዋቅር በከፍተኛ ትኩረት ከተሠሩ መሠረተ ልማቶች ውስጥ አንደኛው ንጹህ የመጠጥ ውሃ የማስፋፋትና ተደራሽ የማድረግ ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሳደግ በርካታ ተዋናዮች መኖራቸውን የጠቀሱት ኃላፊው፤ እነዚህን አካላት በማቀናጀትና በማስተባበር ቅድሚያ ችግሩ በጥልቀት የሚስተዋልባቸው ቦታዎች ላይ የውሃ ፕሮጀክቶች በስፋት መሠራቱን አብራርተዋል።

875 መካከለኛ፣ አነስተኛ እና ጥቃቅን ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ዘንድሮን ጨምሮ በአራት ዓመት ውስጥ ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙም ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 38 አንኳር ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች መሆናቸውን አመላክተዋል።

38ቱ ፕሮጀክቶች እያንዳንዳቸው ከ376 ሺህ እስከ 25 ሚሊዮን ብር ድረስ የግንባታ ወጪ የሚጠይቁ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በድምሩ የ38ቱ ፕሮጀክቶች የግንባታ ውል ሁለት ቢሊዮን ብር መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ውስጥ አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ግንባታውን ለሚያከናውኑ ተቋራጮች የተከፈለ ሲሆን፤ ቀሪው ፕሮጀክቶቹ ሙሉ ለሙሉ እስኪጠናቀቁ ድረስ ይፈጸማል ብለዋል።

ከ38ቱ አንኳር ፕሮጀክቶች ውስጥ 28ቱ ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ኃላፊው ገልጸው፤ እነዚህ አንኳርና ሌሎች ጥቃቅን ፕሮጀክቶች በከፊልና ሙሉ በሙሉ ተጠናቀው አገልግሎት በመስጠታቸው 650 ሺህ 840 የማህበረሰብ ክፍል ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ክልል እንደ ክልል ከተዋቀረ በኋላ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሕዝብ ቁጥሩን ወደ ሦስት ሚሊዮን ገደማ ማድረስ መቻሉን ተናግረዋል።



ብሬንት አድሪያን



ዶክተር ቻርለስ ሙሲባ



ሚርጃና ሮክሳንዲች

# “በአዲስ አበባ የተሰሩት የቱሪስት መዳረሻዎችና የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የከተማዋን ገጽታ ቀይረውታል”

## - የተለያዩ ዓለም ሀገራት ሳይንቲስቶች

**ማርቆስ በላይ**

በአዲስ አበባ፡- የተሠሩት የቱሪስት መዳረሻዎችና የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የከተማዋን ገጽታ ቀይረውታል ሲሉ ከተለያዩ የዓለም ሀገራት መጥተው ከተማዋን የጎበኙ ሳይንቲስቶች ገለጹ፡፡

ሉሲ (ድንቅነሽ) የተገኘችበት 50ኛ ዓመት መታሰቢያ ላይ ለመሳተፍ ከተለያየ ዓለም የመጡ 200 በላይ ሳይንቲስቶች በአዲስ አበባ የቱሪስት መዳረሻዎችንና ፕሮጀክቶችን ትናንት ጎብኝተዋል።

ከአሜሪካ አሪዞና ስቴት ዩኒቨርሲቲ የመጡት ብሬንት አድሪያን ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባ ከተማን የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን የሚያስችሉ የመሠረተ ልማቶች ተሠርተዋል፡፡

በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም፣ በብሔራዊ ሙዚየም እና በአንድነት ፓርክ ጉብኝት ማድረጋቸውን የገለጹት ብሬንት፤ በከተማዋ የተሠሩ የተለያዩ መዳረሻዎች ለጎብኚዎች ምቹ በሆነ መልኩ ተሠርተዋል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ቅኝ ግዛትን አንቀበልም በማለት በዓድዋ ድል ማድረጋቸው ለአፍሪካውያን ነጻነት መነቃቃትን የፈጠረ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ የከፈለችው ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ እየተሠሩ የሚገኙት የኮሪደር ልማትና የመሰረተ ልማት ማስፋፊያዎች የከተማዋን ገጽታ ቀይረውታል ያሉት ብሬንት፤ የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም፣ አንድነት ፓርክ፣ የእግረኛ፣ የሳይክልና የተሽከርካሪዎች መንገዶችን ጨምሮ የሰዎች መዝናኛ ቦታዎችን መመልከታቸውን ተናግረዋል፡፡

ከታንዛኒያ ዱክ ዩኒቨርሲቲ የመጡት ዶክተር ቻርለስ ሙሲባ በበኩላቸው፤ የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም በአህጉሪቱ ከሚገኙ ምርጥ ሙዚየሞች አንዱ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ነጻነት የነበራት አበርክቶ እጅግ ትልቅ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ቻርለስ፤ በተለይም ለኬንያ፣ ታንዛኒያ እና ኡጋንዳ ብሎም ለተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ነጻነት የሀገሪቱ አበርክቶ ትልቅ ነበር ብለዋል፡፡

አዲስ አበባን ከስድስት ዓመት በፊት እንደሚያውቋትና በአሁኑ ጊዜ በርካታ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ከተማዋ እንደለወጡት በመግለጽ፤ በተለይም የከተማዋ ፈጣን የእድገት መጠን፣ የመንገድ፣ የመዝናኛ ቦታዎች፣ የመኪና ማቆሚያዎች በመገንባታቸው በአውሮፓ የምናውቃቸውን ከተሞች መምሰል ጀምራለች ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ ወጣቶች ወደ አውሮፓ መሄድ የለባቸውም፡፡ ሁሉም ነገር በሀገራቸው እየተሠራ ነው ያሉት ዶክተር ቻርለስ፤ ኢትዮጵያ አፍሪካ መሥራት እንደምትችል በግልጽ ማሳየቷንም ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ እየተሠሩ ያሉ ፕሮጀክቶች ከተማዋን የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ የሚያስችሉ ናቸው ያሉት ደግሞ ከካናዳ ዊኒፔግ ዩኒቨርሲቲ የመጡት ሚርጃና ሮክሳንዲች ናቸው፡፡

አዲስ አበባ አሁን ባለችበት ደረጃ ውብ ትሆናለች ብዬ አስቤ አላውቅም ያሉት ሚርጃና፤ የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም፣ ብሔራዊ ሙዚየም፣ አንድነት ፓርክ እና ሌሎችም ፕሮጀክቶች አድናቆትን ፈጥረውብኛል ብለዋል፡፡

ሉሲ የተገኘችበትን 50ኛ ዓመት ለማክበር በመምጣታቸው የተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎችን ለመጎብኘት እድል እንደፈጠረላቸው ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው እንደተናገሩት፤ ሉሲ የተገኘችበትን 50ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ 230 በላይ ሳይንቲስቶች መምጣት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡

ከመርሃግብሩ ጎን ለጎን በአዲስ አበባ የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች፣ 13 ድንቅ ግኝቶችን፣ አንድነት ፓርክ፣ ዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም እና የኮሪደር ልማቶችን ተመልክተዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የኮሪደር ልማቱ መስፋፋትን ተከትሎ አዲስ አበባ እየተቀየረች ለቱሪስት ምቹ እየሆነች ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ያሏትን የተፈጥሮ፣ የባህልና የታሪክ ጸጋዎችን በመለየት መጠቀምና ማስተዋወቅ የጀመረችበት አዲስ ምዕራፍ ላይ መሆኑዋን ጠቅሰው፤ በጉብኝቱ የተሳተፉ ሳይንቲስቶች የኢትዮጵያ የቱሪዝም መዳረሻዎች ማስተዋወቅ የሚችሉ መሆናቸውንም ተናግረዋል፡፡

# ከቅጣት በፊት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እየሆኑ እንደመጡም ትዝብታቸውን ያጋራሉ።

አቶ አምደሚካዔል አድማሱ በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ከፍተኛ የሕገ መንግሥት ተመራማሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፣ በሀገራችን በየጊዜው ጥሩ የሚባል ይዘትና አስፈላጊነት ያላቸው ሕጎች ይወጣሉ። የወጡ ሕጎችን በማክበርና ለሕግ በመገዛት በኩል ግን፣ እንደ ሀገር ጉልህ ችግር አለ። ይህ ደግሞ፣ በሀገር እድገት፣ ሠላምና የፖለቲካ ሥርዓት ላይ በርካታ ችግሮችን ሲፈጥር ይስተዋላል።

የሕገ መንግሥት ተመራማሪው እንደሚሉት፤ እንደ ማኅበረሰብ በሕግ ከመገዛት ጋር በተያያዘ ላሉ ችግሮች ዋና ከሚባሉ ጉዳዮች ቀዳሚው፤ ሕግ ለማውጣት የሚደረገውን ጥረት ያህል ሕግን ለማስፈጸም ያለው ትጋት እምብዛም መሆኑ ነው።

ሌላኛው መሠረታዊ ሆኖ ሊገለጽ የሚችለው ደግሞ፣ የማኅበረሰቡ ንቃተ ህሊና አለማደግ ነው በማለት ይገልጻሉ።

አንድ ሕግ ከወጣ በኋላ በማኅበረሰቡ ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎች ጠንካራ አለመሆናቸው ህብረተሰቡ ሕግን አውቆ እንዳይገዛ አንዱ መንስዔ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

በብዙ ማኅበረሰብ ዘንድ ሕግ ወጣልን ሳይሆን መጣብን የሚል አስተሳሰብ መኖሩንም የሚጠቅሱት አቶ አምደሚካዔል፤ አንድ ሕግ ሲወጣ በብዙ መልኩ ተፈትሾና ተገምግሞ አስፈላጊነቱ ታምኖበት እንጂ ማንንም ለመጉዳት አይወጣም ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ ሕግ ማስከበር ላይ ያሉ አካላት በአግባቡና በታማኝነት ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ከሆነና ብልሹ አሠራሮች ከተበራከቱ ሕዝብ በሕግ ከማመን ይልቅ ሕገወጥነትን አማራጩ አድርጎ የሚወስድ እንደሚሆንም ያብራራሉ።

ለሕግ የተገዛ ማህበረሰብን ለመገንባት በሕግ አስከባሪ አካላት ዘንድ የሚስተዋሉ ብልሹ አሠራሮችን ማስተካከል እንደሚገባም ነው የሚመከሩት።

ሕግን አክብሮ ለሕግ ተገዝቶ መኖር ዘመናዊነት ነው የሚሉት አቶ አምደሚካዔል፤ በዚህ ረገድ በአህጉረ አፍሪካ ደቡብ አፍሪካ፣ ጋና፣ ጥሩ ተሞክሮ ያላቸው ሀገራት ሲሆኑ፣ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ አካባቢ ደግሞ ጠንካራ የሕግ ሥርዓት በመዘርጋቱ ሰው በጤነኛው አዕምሮ ሕግ ይጥሳል ተብሎ የማይታሰብበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ብለዋል።

ይህንን ዘመናዊ አመለካከት ወደ ሀገራችን ለማምጣት ህጻናት ከልጅነታቸው ጀምሮ የሥነ ምግባር ትምህርት ሲማሩ ለሕግ መገዛት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማሳየት ይገባል ይላሉ።

ዜጎች ከቅጣት በፊት ወደውና ፈቅደው ለሕግ የሚገዙበትን አመለካከት በመገንባት ረገድ ሕግ አስፈጻሚው በተለያዩ የሕዝብ መገናኛ መንገዶች ሕግ የማስረጽ ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ ያነሱት የሕገ መንግሥት ተመራማሪው፤ ሕገ ወጥነት ላይ ጠንካራ ርምጃ መውሰድና የሚወሰዱ ርምጃዎችን አስመልክቶ ሕዝቡ በቂ እውቀትና መረጃ እንዲኖረው ማድረግ ላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት እንደሚገባ አስምረውበታል።

በሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ ከፍተኛ የሕገ መንግሥት ተመራማሪ አቶ አቤኔዘር ጥሩአየሁ በበኩላቸው፣ ሕግን ከማክበር ጋር ተያይዞ የሚስተዋለው ችግር ሕግን አለማወቅ ሳይሆን “ሕግን እያወቁ መጣስ ነው” ይላሉ።

ለዚህም ከትራፊክ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ የሕግ ጥሰቶችን አብነት አድርጎ በመጥቀስ፤ በህብረተሰቡ ዘንድ ሕግ ማክበርም ሆነ መብቱን በሕግ ማስከበር ላይ ከፍተኛ የግንዛቤ ችግር መኖሩን ያነሳሉ።

ሌላው ያነጋገርነው በግል የሕግ ማማከር አገልግሎት የሚሰጡት አቶ ኢዘዲን ፈድሉ፣ ሰዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ሕግን የማያከብሩ የሚሆኑበት አንደኛው ምክንያት የማኅበራዊ ውል መላላት ነው በማለት ሃሳባቸውን ይገልጻሉ።

የሀገረ መንግሥት ግንባታ አለመጠናቀቅም እንዲሁ ዜጎች ወደውና ፈቅደው ለሕግ እንዳይገዙ ምክንያት እንደሚሆንም ይጠቅሳሉ።

ግለሰቦች ከሕግ በታች የሆኑባት፣ ሕግ የሚከበርባት ሀገርን ለመመስረት በማኅበረሰብ መካከል ጠንካራ ውል ማበጀት ያሻል ብለውም፤ ይህም የመንግሥት፣ የምሁራን፣ የእምነት አባቶች ብሎም የመላው ህብረተሰብ ኃላፊነት እንደሆነ ይናገራሉ።

ከመንግሥት ሥርዓት ጋር በተያያዘ ዜጎች ሕግ አውጪው የሚያወጣቸውን ሕጎች በራሳቸው ተነሳሽነት የሚያከብሩ እንዲሆኑ፤ ሕዝብ አመኔታ የሚጥልበት እና ሁሉም ወጥ በሆነ መልኩ የሚተዳደርበት ሥርዓትን መቅረጽ ያስፈልጋል ሲሉ ያስረዳሉ።

ዜጎች ሕግን አክብረውና ተከባብረው የሚኖሩ ከመሆናቸው የተነሳ የፖሊስ ኃይል የሌለባቸው አንዳንድ ስካንዲኒቪያን ሀገራት መኖራቸውን የሚያነሱት አቶ ኢዘዲን፤ በእነዚህ ሀገራት ሕግ አስከባሪ ጣልቃ የሚገባው ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ሲፈጠሩ ብቻ መሆኑን በማሳያነት ጠቅሰዋል።

# “የማክሮ ኢኮኖሚ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ምን መደረግ እንዳለበት በጥልቀት መዝነን አስቀምጠናል ብለዋል።

ዓላማችን የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አካሄዳችን ድሃ ተኮር ነው። ትኩረታችን ለችግር በመጠቃት ተጋላጭ የሆኑ ደካሞችን መደገፍ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የለውጥ ሥራዎች ሁሉ ስኬት በባለድርሻ አካላት የተባበረ ጥረት ላይ እንደሚመሠረት ገልጸው፤ ይህም ምርታማነትን፣ የውጭ ንግድን እና ገቢን ተባብሮ ማሳደግ ማለት ነው ብለዋል።

የሕግ አስፈጻሚ አካላት የለውጥ ሥራውን ባልተገባ ሕገ ወጥ መንገድ ለመጠቀም በሚፈልጉ ስግብግብ ነጋዴዎች ላይ ርምጃ እንዲወስዱ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# “እንደ ሀገር ያጣነውን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ ኃይማኖት ተቋማት ኢትዮጵያ በተፈተነችባቸው ጊዜያት ሁሉ አብረው የተፈተኑ የእምነት ብቻ ሳይሆን የማንነትም መገለጫ ጭምር መሆናቸውን ተናግረዋል።

ሀገር ችግር በገጠማት ጊዜ ከፊተና ጀርባ ተስፋ መኖሩን ያመላከቱን ውድ ተቋማት ናቸውም ብለዋል።

የኃይማኖት ተቋማት ለሠላም ግንባታና ለዘላቂ አንድነት ለማዋል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ሥራዎችን በአብሮነት እየሠራ መሆን ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታው፣ የተቋማቱን አቅም ለዘላቂ አንድነት የማዋል ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

እስካሁን ድረስም ያለማንም ትዕዛዝ ለሠላም፣ ለአብሮነትና ለዘላቂ አንድነት እየሠሩ ላሉት የኃይማኖት ተቋማት አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

የጉባዔው የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ሰብሳቢ ሊቀጳጳስ አባ ጎርጎርዮስ ጉባዔው ባለፈው በጀት ዓመት በጉባዔው የበላይ ጠባቂ አባቶችና በጠቅላላ ጉባዔው የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነትንና አደራን ለመፈጸም በርካታ ተግባራት ማከናወኑን ተናግረዋል።

የሰላምና መከባበር እሴትን የሚገነቡ እንዲሁም የተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮችን ለመቀነስ የሚረዱ የተለያዩ የምክክር መድረኮች፣ ሥልጠናዎችና አውደ ጥናቶችን በማካሄድ የተሳታፊዎችን ግንዛቤ የሚያጎለብቱ ሥራዎች መሠራታቸውን አንስተዋል።

በቀጣይም ተመሳሳይ ተግባራትን በመፈጸም እንደ ሀገር የተቀመጡ ዕቅዶችን ለማሳካት ጉባዔው የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚበረክትም አመላክተዋል።

ጉባዔው አባል የኃይማኖት ተቋማትን በማስተባበር ስለሰላም፣ ስለ አብሮነት፣ ስለ ይቅርታ፣ ስለ ፍትህ፣ ስለ በጎ ምግባርና ስለ መልካም እሴቶች በመደበኛነት ለማስተማር በሚያደርገው ጥረት ሁሉም ባለድርሻ አካላት አዎንታዊ ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉለትም ጥሪ አስተላልፈዋል።

የኃይማኖት ተቋማቱ ጉባዔ በበጀት ዓመቱ ላከናወናቸው ተግባራት ከጎኑ ለነበሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እውቅናና ሽልማት ያበረከተ ሲሆን፣ በመርሐ ግብሩ አባል የኃይማኖት ተቋማት መሪዎች፣ ምዕመናንና አጋር ድርጅቶች ተገኝተዋል።



# በገበያ የሚወሰነው...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

መካከል ወደሚወሰንበት የውጭ ምንዛሬ የገበያ ሥርዓት መሸጋገሩ ተጠቃሽ ነው።

ወደ ተግባር የገባው የውጭ ምንዛሬ የገበያ ሥርዓት ላኪዎች እና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪ ለራሳቸው ማስቀረት ያስችላቸዋል። ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠውን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እንደሚያሻሽልም የሚጠበቅ ነው።

ወደ ውጭ የሚደረግ የካፒታል ሂሳብ ፍሰት የተገደበ ቢሆንም፤ የውጭ ምንዛሪ ገበያው ለገቢ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ነጻ መደረጉን መንግሥት አሳውቋል።

በጥቅሉ ውሳኔው የውጭ ምንዛሬ በአቅርቦትና ፍላጎትን ለማመጣጠን፤ የገቢና የወጪ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ዋጋ ከገበያ ጋር እንዲጣጣም እና የሀገሪቱን የዕዳ ክፍያ ሚዛን ለማስተካከል ይረዳል የተባለለት ነው።

ለመሆኑ የውጭ ምንዛሪን ገበያው እንዲወስነው ማድረግ ምን ፋይዳ አለው? ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችና መሻገሪያ መንገዶችስ ምንድን ናቸው?

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር)፤ እንደሀገር የውጭ ምንዛሪ እጥረት ፈተና ሆኖ መቆየቱን ያነሳሉ። በዚህም የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ለማሟላት፣ ገቢ ምርቶችን ለማስመጣትና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳብ እክል ሲፈጥር እንደቆየ ያብራራሉ።

ምርቶችን ከውጭ የሚያስመጡ ነጋዴዎችም የውጭ ምንዛሪ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ጥቁር ገበያን እንዲጠቀሙ ተገድደው እንደነበረ ጠቁመው፤ ይህም የትርፍ ህዳጋቸው እንዲጠብና ማህበረሰቡ ላይም የዋጋ ንረት እንዲከሰት ምክንያት ሆኖ ቆይቷል ይላሉ።

የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ በገበያ መወሰን ባንኮች የዶላር አቅርቦት እንዲኖር እና በሕገወጥ የምንዛሬ አቅራቢዎች ዘንድ ገበያው ጋር ያለው ሰፊ ልዩነት እንዲጠብ ለማድረግ ያስችላል ያሉት ይንገስ ዶ/ር፤ ወደውጭ የሚላኩ ምርቶችን ዋጋ እንዲጨምር እንደሚያግዝም ያብራራሉ።

ፖሊሲውን በታሰበው ልክ መተግበር ከተቻለ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲያድግ ያደርጋል የሚሉት ይንገስ (ዶ/ር)፤ ወጪ ንግድን በማበረታታትም ከፍተኛ የዶላር ክምችት እንዲኖር ያደርጋል። ነጋዴዎችም በቀላሉ የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ ያስችላል ይላሉ።

ይሁን እንጂ የዶላር ዋጋ መጨመርን ምክንያት በማድረግ ሀገራዊ ምርትና አገልግሎቶች ላይ አላግባብ የሆነ የዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር መንግሥት ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት መፍጠር እንደሚገባው ይጠቁማሉ።

ሀገሪቱ ላይ የሚታየው የፖለቲካ ትኩሳትና የሰላም እጦት ተንቀሳቅሶ ለመሥራትም ሆነ ምርትና ምርማነት ላይ እክል በመፍጠር ለትግበራው እንቅፋት ሊሆን የሚችልበት እድል ሰፊ ነው የሚሉት ምሁሩ፤ ሀገራዊ ፖለቲካው ላይ በሚኖር ልዩነት ምክንያትም ከውጪ የሚላከው ገንዘብም በሚፈለገው ልክ እንዳያድግ ሊያደርግ እንደሚችል ይጠቁማሉ።

መንግሥት ዘላቂ ሰላምን ማስፈንና በብድር እና በርዳታ የተገኘው ሀብትም የሀገር ኢኮኖሚና የሕዝቡን ሕይወት መቀየር በሚችሉ ፕሮጀክቶች ላይ መዋል የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ ሊሠራባቸው የሚችሉ ተግባራት መሆን እንዳለባቸውም ያስረዳሉ።

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህሩ ሀብታሙ ለገሰ ከላይ በተነሳው ሃሳብ ይስማማሉ።

ሆኖም የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ በገበያ እንዲወሰን መደረጉም ጥቅምም ስጋቶችም ይኖሩታል የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ስኬታማነቱም መንግሥት በሚወስዳቸው ርምጃዎችና በፋይናንስ ተቋማት ጥንካሬ ይወሰናል ባይ ናቸው።

መንግሥት እና ብሔራዊ ባንክ የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ ለንግድ ባንኮች የሚያጋሩ ከሆነ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶችና ከውጭ ዕቃ የሚያስመጡ ነጋዴዎች በቀላሉ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ያስችላቸዋል። ይህም የምርቶችና የአገልግሎቶች ዋጋ እየቀነሰ እንዲሄድ ሊያደርግ የሚችል መሆኑን ይጠቅሳሉ።

ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደነበረው በባንክ በቂ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ሳይቻል ቀርቶ ወደ ሕገወጥ ምንዛሬ ገበያ የሚሄዱ ከሆነ የዋጋ ንረቱ ሊባባስ የሚችልበት ዕድል መኖሩንም በስጋትነት ያነሳሉ።

ብሔራዊ ባንክ በብድርም ሆነ በሌላም መንገድ ከሚያገኘው ዶላር ላይ ቢያንስ ሁለት ቢሊዮን ዶላር እንኳን ወደኢኮኖሚው እንዲገባ ቢያደርግ ነጋዴዎች በቂ ዶላር እንዲያገኙና ጥቁር ገበያው እንዲሸነፍ ማድረግ ይቻላል ሲሉም ያስረዳሉ።

ይህም ገበያውን በሂደት የሚያረጋጋ፤ ኢንቨስተሮችን የሚያበረታታ እንዲሁም በሕጋዊ መንገድ ወደሀገር የሚላከውን የውጭ ምንዛሪም እንዲያድግ የሚያደርግ ነው ይላሉ።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ባንኮች የውጭ ምንዛሪን በራሳቸው እንዲፈልጉ የሚተው ከሆነ ግን ጥቁር ገበያው እንዲጨምርና የዋጋ ንረቱም እንዲባባስ ያደርጋል ሲሉ ስጋታቸውን ይገልፃሉ።

የብር ዋጋ እንዲቀንስ ካደረጉ ምክንያት አንዱ ኢኮኖሚው ከሚያመርተው በላይ ከፍተኛ ብር መኖር ነው የሚሉት ባለሙያው፤ ኢኮኖሚው ላይ ብሔራዊ ባንክ የጀመረውን ሰነዶችን ለንግድ ባንኮች እየሸጠ ገበያ ውስጥ ያለውን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር አጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት ይመክራሉ።

እነዚህን ርምጃዎች በአፋጣኝ መውሰድ ካልተቻለ ግን ማህበረሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጫና ሊያሳድር እንደሚችል ስጋት አላቸው።

የፋይናንስ ተቋማት ከሚያከናውኑት ሥራ ጎን ለጎን አስፈጻሚ አካላት የቁጥርና ክትትል ሥራውን አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ይጠቅሳሉ።

ከዚህም በተጨማሪ መንግሥት ማህበረሰቡ ላይ ጫና እንዳይፈጠር የነዳጅ ድጎማ ሥርዓቱን ማሳደግ እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ማህበረሰቦች አስፈላጊውን ድጎማ ማድረግ እንደሚኖርበት ያብራራሉ።

በረጅም ጊዜ ደግሞ የግል ዘርፉ የማይገባባቸውን እና ማህበረሰቡ በዋናነት የሚቀምባቸው ዘርፎች እየለየ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ማድረግ እና በሂደትም የግሉ ዘርፍ እንዲረከበው መሥራት ይጠበቅበታል ይላሉ።

እንደባለሙያዎቹ ማብራሪያ፤ የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ በገበያ መወሰን ጥቅም እንዳለው ሁሉ ስጋቶችም ይኖሩታል። ይህም መንግሥት በሚወስዳቸው ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ላይ ይወሰናል።

በመሆኑም መንግሥት የውጭ ምንዛሬ የገበያ ሥርዓት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይገባዋል።

የሚገኙ ርዳታና ብድሮችንም ቀጣይነት ያለው ሀብት ሊያፈሩ በሚችሉ ፕሮጀክቶች ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

ዘላቂ ሰላምን በማስፈን ምርትና ምርማትን ማሳደግ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን እንዲሁም የወጪ ንግድ ሥርዓትን ማጠናከርም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ውሳኔው ሸቀጦችን በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ በብዙ አማራጮች ማግኘት የሚያስችል ነው!

መንግሥት የንግድ ዘርፉን ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪ እና ፍትሐዊ እንዲሆን ለማስቻል የተለያዩ የፖሊሲ ርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል። በተለይም የሀገሪቱን የንግድ ዘርፍ በራሱ ጊዜ እና አቅም ወደሚፈለግበት ደረጃ እንዲደርስ ለማስቻል ሰፊ ጥረቶችን አድርጓል። ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታትም ለዚሁ ሲባል ለዘርፉ በፖሊስ ደረጃ ከፍተኛ ጥበቃ ሲያደርግ ቆይቷል።

ይህም ሆኖ ግን ዘርፉ እንደ ሀገር ወደሚፈለገው ደረጃ ከመድረስ ይልቅ፣ በተለያዩ ሕገወጥ አስተሳሰቦች እና አሠራሮች ተጠላልፎ፣ የመላው ሕዝባችንን ሕይወት በከፋ ሁኔታ እየፈተነ፤ ላልተገባ እሮሮ እና ችግር ሲዳርገው ቆይቷል። አሁንም በተመሳሳይ መልኩ እየተፈታተነው ይገኛል ።

በሀገሪቱ ኮሽታ በተሰማ ቁጥር ሸቀጦችን ከመደበቅ ጀምሮ፣ ያልተገባ የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ የሕዝባችንን አጠቃላይ የዕለት ተዕለት ሕይወት ችግር ውስጥ ከቷል፣ የሀገር ኢኮኖሚ ፈተና መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል። ሁኔታውን ለመቆጣጠር የሚደረጉ ጥረቶችም ሀገራዊ ከሆነው የመቆጣጠር አቅም ውስንነት ጋር ተዳምሮ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖ ቆይቷል ።

ችግሩ መንግሥት ከፍተኛ የሕዝብ ሀብት አውጥቶ በሚደጉማቸው ሸቀጦች ላይ ሳይቀር በስፋት ሲስተዋል ቆይቷል። ይህ ኃላፊነት በማይሰማቸው የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ዘንድ እየተስተዋለ የመጣው፤ ከአጠቃላይ ከሕዝባችን ባሕል እና ወግ ያፈነገጠ ራስ ወዳድነት፣ ሕዝብ ጥራታቸው የተጠበቁ ሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንደ አቅሙ አማርጦ እንይገዛ ፈተና ሆኖበታል።

ከሁሉም በላይ መንግሥት የንግዱ ዘርፍ በሀገር ውስጥ ተዋንያን እጅ ሳይወጣ ዘርፉን ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪ እና ፍትሐዊ እንዲሆን በፖሊሲ ደረጃ ሲያደርግ የነበረው ጥበቃ ትርጉም የለሽ እንዲሆን አድርጎታል። ፖሊሲው በዘርፉ ተዋንያን የተሳሳተ እሳቤ መንገድ ስቶ አጠቃላይ የሆነውን የዘርፉን ዕድገት በብዙ እንዲቀጭጭ እና ሕዝብም አላስፈላጊ ዋጋ እንዲከፍል አድርጎታል ።

ከዚህ የተነሳም ዓለም በብዙ አማራጮች ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪ እና ፍትሐዊ የገበያ ሥርዓት ፈጥራ፣ ብዙዎች የዚህ ተጨባጭ ዓለም አቀፋዊ እውነታ ተጠቃሚ እየሆኑ ባሉበት ሁኔታ፣ ኢትዮጵያውያን ግን የዘርፉ ተዋንያን በፈጠሩት የተዛባ አስተሳሰብ እና ራስ ወዳድነት የተነሳ፣ በሚፈጠረው ያልተገባ ጫና ብዙ ዋጋ ለመክፈል የተገደዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ይህንን ችግር ለመፍታት በመንግሥት በኩል የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፣ ችግሩ በአስተሳሰብ ሆነ በአሠራር ደረጃ ካለበት አስቸጋሪ ደረጃ አኳያ፣ ጥረቶቹ በሚጠበቀው ደረጃ ውጤታማ መሆን ሳይችሉ ቀርተዋል። እንዲያውም መሽቶ በነጋ ቁጥር አዲስ የችግር አቅም እያጎለበቱ የሕዝባችንን ሮሮ ከማባበስ አልፈው ዋነኛ የሕይወቱ ፈተና ሆነው ቀጥለዋል።

ይህን ችግር ለመፍታት በቅርቡ መንግሥት የሀገሪቱን ንግድ ነፃ (ሊበራላይዝድ) ማድረግ የሚያስችል የፖሊሲ ለውጥ አድርጓል። በዚህም ለንግዱ ዘርፍ ሲያደርግ የነበረውን የፖሊሲ ጥበቃ በማንሳት ዘርፉ በተወሰነ ደረጃ ለዓለም አቀፍ ገበያ ክፍት እንዲሆን ወስኗል። የፖሊሲ ለውጡ ከሁሉም በላይ ሕዝባችን ሸቀጦችን በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ በብዙ አማራጮች ማግኘት የሚያስችለውን ዕድል የሚፈጥርለት እንደሚሆን ይታመናል።

ሕገ ወጥ ነጋዴዎችም ከቀደመው ያልተገባ መንገዳቸው ተመልሰው በኃላፊነት መንፈስ፣ ተወዳዳሪነትን መሠረት ባደረገ የንግድ ሥርዓት ተገርተው፣ ሀገራቸውን እና ሕዝባቸውን በታማኝነት ማገልገል የሚችሉበትን መልካም አጋጣሚ ለመፍጠር ይረዳል፣ በቀጣይም በተጀመረው ሀገራዊ ለውጥ የንግዱ ማኅበረሰብ የራሱን ትርጉም ያለው ዐሻራ እንዲያሳርፍ የተሻለ አቅም እንደሚፈጥርለትም ይታመናል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በቅርቡ ወደ ሙሉ ትግበራ የገባው የሀገሪቱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲም፤ ይህንን እንደሀገር የጀመርነውን የንግዱን ዘርፍ ሊበራላይዝድ የማድረግ እንቅስቃሴ ዋንኛ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በንግዱ ዘርፍ ብዛት ያላቸው ዓለም አቀፍ ተዋንያን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የተሻለ ዕድል መፍጠር የሚያስችል ነው፡፡

በተለይም የውጪ ምንዛሪ በገበያ እንዲመራ የሚደነግገው የመንግሥት ውሳኔ፣ በዘርፉ ገዝፎ የነበረውን ሕገወጥነት በማስቀረት፣ ሕዝባችን ሸቀጦችን በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ በብዙ አማራጮች ማግኘት የሚያስችለውን የተሻለ አማራጭ የሚፈጥር፤ የንግድ ዘርፉን ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪ እና ፍትሐዊ እንዲሆን የሚያስችል ነው!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ገበያ መር የውጪ ምንዛሪ

**ምሕረት ሞገስ**

ከሰሞኑ መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራምን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት አሻሽሏል። የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ የውጭ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል በሚወስንበት የገበያ ሥርዓት ላይ የሚመሠረት ነው። ይህ ማለት የውጪ ምንዛሪው ወይም በብርና በዶላር መካከል ያለው ልዩነት የሚወሰነው ፍላጎት እና አቅርቦት ላይ ተመሥርቶ ነው ማለት ይቻላል። በአጭሩ ለማስረዳት ያህል ሸንኩርት በስፋት ሲገባ እንደሚረክሰው ሁሉ ዶላር ሲበዛ የምንዛሪ ዋጋው ይቀንሳል ማለት ነው። ይህ በተዘዋዋሪ እንደሁኔታው የብር የመግዛት አቅም የሚያድግበትም ሆነ የሚቀንስበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

ይህ መንገድ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከቅርቧ ኬኒያ ጀምሮ በግብፅ እና በደቡብ አፍሪካ እንዲሁም በሌሎች ሃገሮች እየተተገበረ ያለ አዋጭ መንገድ ስለመሆኑ የዘርፉ ምሑራን ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ማሻሻያ ዙሪያ ብዙዎች የተለያዩ ሃሳቦችን በመሰንዘር ላይ ይገኛሉ። ከሃሳቦቹ መካከል የውጪ ምንዛሪው ዋጋ የሚዋዥቅና በከፍተኛ ደረጃ የሚለዋወጥ ባሕርይ ስለሚኖረው የምንዛሪ ተመኑ አሳሳቢ ይሆናል የሚለው አንደኛው ነው። ነገር ግን በመንግሥት በኩል በዚህ ላይ ቀድሞ እንደታሰበበት እየተገለፀ ይገኛል። እዚህ ላይ ዋጋውን ለማረጋጋት ብሔራዊ ባንክ ትልቁን ሚና ይጫወታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሚና ገበያውን በማረጋጋት ላይ ያተኮረ ነው ሲባል፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዶላር ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ሲንር ገበያውን ለማረጋጋት ለገበያው ዶላር ያቀርባል። በተቃራኒው ደግሞ ዶላር ሲረክስ ከገበያው ላይ ዶላር ይገዛል። በእዚህ መንገድ ገበያው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን መዘበራረቅ ለማስተካከል ጥረት እንደሚደረግ ታውቋል። ይህን መሠል አሠራር በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለማችን ላይ በትልልቅነታቸው ታዋቂነትን ያተረፉት የአሜሪካን፣ የኬኒያ፣ የደቡብ አፍሪካም ሆኑ የግብፅ ባንኮችም በውጪ ምንዛሪ ላይ ሚናቸው ዋጋን ከማረጋጋት የዘለለ አይደለም።

ማሻሻያውን ተከትሎ ቀደም ሲል ሲሠራ እንደነበረው የውጭ ምንዛሪን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ቀሪ መሆኑን መንግሥት አሳውቋል። በመሆኑም፣ ላኪዎችና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪ ለራሳቸው በማስቀረት የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ችግራቸውን በራሳቸው መንገድ ያሻሽላሉ። ይህ ብቻ አይደለም፤ ያገኙትን ዶላር ሃገር ውስጥ በማስገባት በግማሽ ብር በመዘርዝር እየተጎዳን ነው ከሚለው ሮሮ በመውጣት እና ዶላር ወደ ውጪ ከማሸሽ ይልቅ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያ የውጪ ምንዛሪ የምታገኝበት ዕድል ይጨምራሉ።

በተለይም ትላልቅ ላኪዎች ውስጥ ውስጡን የሚታሙበት እና እስከ አሁን ፈተና ሆኖ የቆየው ዶላርን፣ ፓውንድን ወይም ዩሮንም ሆነ ድርሃምን ካገኙ በኋላ ወደ ሃገር ውስጥ ከማስገባት ይልቅ በገበያ ላይ የተሻለ ዋጋ ስለሌላቸው ዶላሩን ዱባይ የሚያስቀምጡበት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እንዲቀር ያግዛል የሚል ተስፋም ተይዟል። በተጨማሪ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ያገኙትን ምንዛሪ ወደ ሃገራቸው ከማስገባት ይልቅ እዛው በማስቀረት፤ ኢትዮጵያውያን ከውጪ የሚልኩትን ምንዛሪም እዛው አስቀርተው በጥቁር ገበያ በብር ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ የሚሰጡበት ሁኔታም ይቆማል።

ከዚህ በኋላ የገንዘብ ምንዛሪው ተመጣጣኝ ስለሚሆን፤ ውጪ በመመንዘር ለራስ በማድላት ሃገርን የመጉዳት ተግባር ይቆማል። ነጋዴዎች ውጪ ሃገር በጥቁር ገበያ ገንዘብ የመላክ ሥራውን ሲያቆሙ፤ ሰዎች በባንክ የሚልኩበት ሁኔታ ይፈጠራል። በተጨማሪ ውጪ ሃገር ያሉ ሰዎችም በጥቁር ገበያም ሆነ በባንክ በሁለቱም ቢልኩ ዋጋው ተመሳሳይ ስለሚሆን በባንክ የሚልኩ በመሆናቸው የውጭ ምንዛሪው ቀጥታ ወደ ሃገር ውስጥ ይገባል። ይህ ፈተና ሆኖ የቆየውን የኢትዮጵያ የውጪ ምንዛሪ እጥረትን ለማቃለል ያግዛል።

**ከዚህ በኋላ የገንዘብ ምንዛሪው ተመጣጣኝ ስለሚሆን፤ ውጪ በመመንዘር ለራስ በማድላት ሃገርን የመጉዳት ተግባር ይቆማል። ነጋዴዎች ውጪ ሃገር በጥቁር ገበያ ገንዘብ የመላክ ሥራውን ሲያቆሙ፤ ሰዎች በባንክ የሚልኩበት ሁኔታ ይፈጠራል**

በሌላ በኩል ቡናን ጨምሮ ቅመማ ቅመሞች እና ሌሎችም ከኢትዮጵያ ወደ ውጪ የሚልኩ ሰዎች ወደ ውጪ ሲልኩ የሚያገኙት ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ ወደ ውጪ ከመላክ ይልቅ በሃገር ውስጥ የመሸጥ ዝንባሌ በተደጋጋሚ ታይቷል። ይህ ሃገሪቱ ማግኘት የምትችለውን የውጪ ምንዛሪ የሚያስቀር ከመሆኑም ባሻገር ገበያን እየረበሹ ጮሌው ነጋዴ ሲከብር፤ ሕጋዊ መስመርን የተከተለው ነጋዴ ሲከብር ተስተውሏል። በመሆኑም ማሻሻያው እንዲህ ዓይነቱን ኢ-መደበኛ አሠራር በማስቀረት በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ፣ ግልጽና አመቺ ወደሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ለመግባት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥርም የዘርፉ ምሑራን እየገለፁ ይገኛሉ፡፡

በተጨማሪ ሰሞኑን የተካሄደው የውጪ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት ዕድገትንም ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑም ተጠቁሟል። ቀደም ሲል ለጥሬ ዕቃ ግዢም ሆነ ለሠራተኛ ደመወዝ ከፍተኛ ዶላር ያስፈልግ ስለነበር የውጪ ኢንቨስተር ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ የሚያለማበት ሁኔታ የተወሰነ እንደነበር የሚካድ አይደለም። ከዚህ በኋላ ግን አንድ ኢንቨስተር በውስን ዶላር የሠራተኛ ደመወዝን ጨምሮ ብዙ ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልጉ ወጪዎች ስለሚሸፈንለት ብዙ የውጪ ኢንቨስተሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ለመሥራት ይነሳሳሉ፡፡

በጥቅሉ፣ የውጪ ምንዛሪ ማሻሻያው የውጪ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ሌሎች የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ በርካታ የለውጥ እርምጃዎችን ለማጠናከር የሚረዳ ቢሆንም፤ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት መዘንጋት አይገባም።

መወሰድ ስላለበት ጥንቃቄ ሲነሳ፤ ማሻሻያውን ተከትሎ የዋጋ መናር ሊያጋጥም የሚችል በመሆኑ ያንን ለመቆጣጠር አቅርቦት ላይ በስፋት መሥራት እንደሚገባ ተጠቁሟል። በተጨማሪ የማሻሻያውን ዜና ተከትሎ ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጋዘን ውስጥ ምርት በማከማቸት እጥረት ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ላይ የተጀማመሩ ቁጥጥሮች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

የውጪ ምንዛሪ የመግዛት አቅም መጎልበትና የብር የመግዛት አቅም መዳከም ከምርት እጥረት ጋር ተያይዞ በተለይ ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ ዜጎች ሊፈጥር የሚችለው ጫና ከፍተኛ በመሆኑ፤ መንግሥት ገቢያቸው አነስተኛ ለሆኑ ጡረተኞችም ሆነ የመንግሥት ሠራተኞች ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ሊታሰብ ይገባል፡፡

በሂደት በተለይ በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ አስተማማኝ የምርት አቅርቦት ሊኖር ይገባል። አቅርቦት በስፋት ካለ የዋጋ መናር ዕድሉ አነስተኛ ስለሚሆን፤ የመሠረታዊ ሸቀጦችን ምርት የማስፋት ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ይህ ሁሉ ጥንቃቄ ከተደረገ ማሻሻያው የሚያስገኘው መልካም ውጤት ከፍተኛ እንደሚሆን አያጠያይቅም። ሠላም!

# ነፃ ሃሳብ

# ስለ ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲው ጭፍን ድምዳሜና ችኩል አጠቃሎን እናስወግድ

ታምራት ተስፋዬ

በ20ኛው ክፍለ ዘመን ዓለማችን ከተመለከተቻቸውና የኢኮኖሚክስን መልክና ቁመት እንዲሁም አቅጣጫ ካስተካከሉ ስመጥር ምሁራን አንዱ ስለመሆናቸው በርካቶች በአንድ ድምፅ ይስማማሉ። አሜሪካዊ ናቸው። ውልደታቸው እኤአ በ1912 ነው። በገቢ እና በፍጆታ ላይ ባደረገው ጥናት እኤአ በ1976 በኢኮኖሚክስ ዘርፍ የኖቤል ሽልማት ተቀብለዋል። እኚህ ታዋቂ ኢኮኖሚስትና የስታትስቲክ ምሁር ሚልተን ፍሬድማን ይባላሉ፡፡

ሰውየውን ምንጊዜም አይረሴ ከሚያደርጋቸው ጥናትና ምርምሮች ባሻገር በተለየ እይታና አስተያየታቸውም ይታወቃሉ። ከአስተያየቶቻቸው መካከልም «ማናቸውም የምጣኔ ሀብት ፖሊሲዎች መተቸት ያለባቸው በውጤታቸው እንጂ በሃሳባቸው መሆን የለበትም «One of the great mistakes is to judge policies and programs by their intentions rather than their results.» የሚለውን አንደኛው ነው። ይህ አስተያየት በአግባቡ የተረዱም ከወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ማስተሳሰር አይከብዳቸውም፡፡

እንደሚታወቀው፣ ኢትዮጵያ ከቀናት በፊት ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ትግበራ ገብታለች። መንግሥት አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራምን አስመልክቶ በሰጠው መግለጫም፣ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ቁልፍ ዓላማዎችና ግቦች መካከል የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ማስተካከልና የረጅም ጊዜ የውጭ ክፍያ ሚዛን ጉድለት ችግሮችን መፍታት አንዱ ነው። የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፉን በማዘመን የዋጋ ንረትን መቀነስና የዕዳ ተጋላጭነትን በመፍታት፣ የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግና ሀገራዊ የልማት ፍላጎቶቻችንን በሀገር ውስጥ አቅም ለማሳካት ምቹ መደላድል መፍጠር ሌሎቹ ግቦች ናቸው።

በተጨማሪ የፋይናንስ ዘርፉን አካታችነት፣ ተወዳዳሪነትና ጤናማነት ማጠናከር እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም እና የምግብ ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ፤ ጠንካራ፣ አካታችና ዘላቂ የኢኮኖሚ ሥርዓትን መገንባት ግቦቹ መሆናቸው ተመላክቷል፡፡

የፖሊሲ ርምጃዎቹ ከአጠቃላይ ሀገራዊ የረጅምና የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶቻችን ጋር ተጣጥመው ይከናወናሉ። እንዲሁም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ እና የዜጎቻችንን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲተገበሩ መንግሥት ከፍተኛ የክትትልና የድጋፍ ማዕቀፎችን እንደሚዘረጉ ተጠቁሟል።

ለዚህም በሁሉም በሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና በመንግሥታዊ ተቋማት በኩል አስፈላጊ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። በሁሉም በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል የፖሊሲ ትግበራ አፈጻጸም ወጥነት እንዲኖር መንግሥት ጠንካራ የፖሊሲ ማሻሻያ አመራር መኖሩን ያረጋግጣል ብሏል፡፡

መንግሥት ያሳለፈውን ውሳኔ ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻሉን አስታውቋል። አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው የገበያ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባና ኢ-መደበኛ አሠራር በማስቀረት ተወዳዳሪ፣ ግልጽና አመቺ ወደሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መግባትን የሚያበረታታ እንደሆነ ነው የገለጸው።

ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ሌሎች የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ በርካታ የለውጥ ርምጃዎችን ለማጠናከር እንደሚረዳም አመላክቷል።

ለፖሊሲው ስኬታማነት የሚወሰዱ ርምጃዎች ሰፊና በቂ ቅድመ ዝግጅት እንደተደረገም በሕዝቡ በተለይም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማቃለል የአንዳንድ መሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ በጊዜያዊነት ለመደጎምና እንዲሁም የገንዘብ ድጎማ ለመስጠትም መወሰኑን ገልጿል፡፡

ይህ የፖሊሲ ማሻሻያ መደረጉም ተከትሎም ከአቅጣጫው የተለያዩ አስተያየቶች በመዥጎድጎድ ላይ ናቸው። ከላይ በመግቢያችን እንደጠቀስነው «ማናቸውም የምጣኔ ሀብት ፖሊሲዎች መተቸት ያለባቸው በውጤታቸው እንጂ በሃሳባቸው መሆን የለበትም። የአንድን ፖሊሲ ውጤት ለመረዳት ደግሞ ጊዜ መስጠት የግድ ነው። አንድ መድኃኒት ሊያሽርም ሆነ ላያሽር የሚችለው አስቀድሞ ሲወሰድ ነው። ከተወሰደ በኋላ ውጤቱን ለመገምገም የተወሰነ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ አያከራክርም።

አንድን ሃሳብ፣ ውሳኔ ብሎም ፖሊሲ ማድነቅም መተቸትም ተገቢ ነው። የልክነት ትርጉሙና ፍቺው በአንድም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲታሰብ ደግሞ ማሰብ ብቻም ሳይሆን በምክንያት መሳብ ጋር ተያይዞ ይመጣል። ምክንያታዊነት ደግሞ በተንኮል ያልታጠፈ፣ በምቀኝነት ያልተቆለመመ፣ በራስ ወዳድነት ያልተንጋደደ ሃሳብና ምግባር ነው። ምክንያታዊነት፣ አመዛዛኝነት፣ አስተዋይነት ነገሮችን አንድ በአንድ በጥልቀት በማየትና በመመርመር እውን የሚሆን ነው። እንደ ሃሳብ ሁሉ የማንኛውም ፖሊሲ ትክክለኛ ምስል ለማግኘት ሚዛናዊና ምክንያታዊ መሆን፣ ከሁሉ በላይ ከጭፍን ድምዳሜና ችኩል አጠቃሎ መራቅ የግድ ይላል፡፡

ከሰሞኑ ውሳኔ ጀርባ የሚሰሙ ጩኸቶች ግን ከዚህ እሳቤ በእጅጉ የተራራቁ ሆነው በመደመጥ ላይ ናቸው። በርካቶች ውሳኔውን የደረጃው ከመረዳትና ከመገምገም እንዲሁም ትችትም አስተያየትም ከመስጠት ይልቅ ከጭፍን ድምዳሜና ችኩል አጠቃሎ ውስጥ ገብተው ታይተዋል፡፡

ስለ ውሳኔው አዎንታዊ ጎኑ የሚመሰክሩትን ይህል አሉታዊ መልኩ የሚታያቸውም በርካቶች ናቸው። በተለይ «እኛ ከሌለንበት» የሚሉ፤ ከመተቸት ቅርብ የሆኑ ግላዊ የልዩ ፍጡርነት ስሜት false or wrong self-perception ሰለባዎች እዚህም እዚያም እየጮሁ ናቸው፡፡

በተለይ በኢትዮጵያ እድገት የሚከስሩ፣ በውድቀቷ የሚያተርፉ የዘመናት የሕዝቦች ጥያቄና ፍላጎት የሆነውን ሁለንተናዊ እድገት የመትከልና የማጽናት ትግልን ለመቀልበስ የሚጥሩ ከተደበቁበት ብቅ ብቅ ብለዋል። ለውሳኔው ሁለንተናዊ ውጤታማነት እገዛ ከማድረግ ይልቅ ከውስጥም ከውጭም በባዕዳን ነዋይ ተደልለው በገዛ ሀገራቸው ላይ የጸረ አንድነት መፈክር የሚያሰሙ አልሞት ባይ ተጋዳዮችም ትግላቸውን ቀጥለዋል፡፡

የሰሞኑን የፖሊሲ ውሳኔ ሁለንተናዊ ፋይዳ በቅጡ ከመረዳት ይልቅ በጭፍን ድምዳሜና ችኩል አጠቃሎ የተጠመዱና ስለፖሊሲው ጠንቅቆ ለመረዳት የተዘጉና የተገዘቱትም ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም። ቀድመው የሰሙትን አምነው የተቀበሉና በተቃውሞ ሃሳባቸው ዋሻ መሽገውና የሚዛን በራቸውን ዘግተው የተቀመጡ በርካቶች ናቸው፡፡

በትንሹ ተረድተው በትልቁ የሚፈርዱ መናገር የህልውናቸው ምስክር ወይም ማረጋገጫ አድርገው የሚወስዱና ካልተናገሩ የሌሉ የሚመስላቸው፣ ስለተመለከቱትም ሆነ ስላደመጡት እንዲሁም ስላነበቡት ምንነቱን በቅጡ ያልተረዱ፣ ብቻ በሩቁና በጭፍን የሚደመድሙና በአቃቂር ጫፍ የደረሰም አሉ፡፡

የፖሊሲው ሁለንተናዊ ፋይዳ መረዳት ፈልገው በአግባቡ የሚያስረዳቸው ያላገኙም በርካቶች ናቸው። ይሁንን ከዚህ በአንፃር ሆን ብለው ፖሊሲው ተግባራዊ ቢሆን ሊያጡት የሚችሉትን ሂሳብ በመሥራት «ለምን እየሰረቅን እየዘረፍን አንኖርም?» የሚል ትልቅ ህፍረትና ህሊና ቢስ ጥያቄና ሙግት የሚገጥሙ፣ ኢትዮጵያን ለመዝረፍ፣ ለማስለቀስ፣ ድህነት መስቀል ላይ ቸንክረው ለማሳቃየት የሚተጉም እዚህም እዛም አሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች እንዴት እንዲህ ይሆናል ሲሉ እንዴት እንዲህ አይሆንም ለሚለው ቦታ የላቸውም። ሃሳብ፣ ተግባርን ህልማቸው ቡድናዊ፣ በደንብ ሲጠና ደግሞ ግላዊ ነው። በቀላሉ መታዘብ እንደሚቻለው ከሆነ ምክንያት አልባዎች የአንድን ውሳኔ ጥቅምና ጉዳቱን ፈልቅቆ ለማግኘት አቅምም፣ ዝንባሌም ሆነ ፍላጎቱ ሲያጥራቸው መታዘብ ቀላል ነው፡፡

አለን የሚሉት የእሳቤ ማስረጃም በአብዛኛው ከዕውቀት ጋር ያልተዋሀደ ነው። ስለሚያወግዙት ግማሽ መንገድ ተራምደው አይጠይቁም። ማጣጣል እንጂ ማድነቅ ምርጫቸው አይደለም። የምክንያት አልባነት ሰለባ ተጠቂዎች እንዲህ ብናደርግ ሲባሉ ቢያንስ ሞክረው ውጤቱን ለመመልከት አዋጭ ከሆነ መቀጠል ካልሆነም ለማቋረጥ ዝግጁና ተባባሪነት አይታይባቸውም። ይልቁንም ሳይጀምሩ ይጨርሳሉ፡፡

ይህን ጫና ከፍ ሲልም ፕሮፖጋንዳ ተከትሎም በውሳኔው የተናጡና የሚደናገጡም እዚህም እዛም ይታያሉ። ይሁንና የመንግሥት ውሳኔ ያማረ ነው ወይስ የመረረ ለማለት አስቀድሞና ጊዜ ሰጥቶ መቅመስ ከፍ ሲልም ማጣጣም ግድ ይላል። ይህ ደግሞ መረጋጋትን ይጠይቃል። ጊዜም ይፈልጋል፡፡

ይሁንና አንድ ሊሰመርበት የሚገባው ሃቅ ቢኖር እኛ ያልነው ብቻ ልክ ነው ሌሎችን አትስሙ በሚል ትችት ብቻ ማዝነብ፣ ከግዙፉ ነጭ ይልቅ ነጥቧን ጥቁር በማጉላት የሀገርን የብልፅግና ጉዞ ለማድነቅ የድንጋይን ሚና መያዝ ተገቢ አይደለም። እንዲህ ብንደርግስ፣ እንዲህ ሊደረግ ታስቧል እንዲህ ተደረገ በተባሉ ቁጥር ለጭፍን ድምዳሜና ችኩል አጠቃሎ መቸኩር ጤነኝነት አይደለም። መሰል ምክንያት አልባነትና ጭፍን ድምዳሜ ምንም አይለውጥም። አይቀይርም። አያዘምንም። አያሰለጥንም። ለማወቅ ለመመርመር፣ ለመሰልጠን አዳዲስ መንገዶችን ለመፈተሽ ዕድል አይሰጥም። ማንንም አያስተምርም።

ሕዝብም ቢሆን መሰል ውሳኔዎች በተላለፉ ቁጥር ቶሎ ብሎ ወደ መራድ የሚሄድ ከሆነ በመሠረቱ ትክክል አይደለም። በጭፍን ድምዳሜና ችኩል አጠቃሎ ከመዋጥና ከመደናገጥ ይልቅ የፖሊሲው አሉታዊና አዎንታዊ ጎን ምንድነው፣ ከመልካሙ ለመጠቀም ከመጥፎው ለመሸሽ ምን ማድረግ ይገባል የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ለመልሱም በአግባቡ ስለ መዘጋጀት መጨነቅ አዋጭ ነው።

ከዚህ ባለፈ ገና በጠዋቱ ሃሳቡ ተግባራዊ በሆነበትና ውጤቱ ባልታየበት ሁኔታ መሸበር እንድንወድቅ ለሚፈልጉ መመቸት መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ነው። ይህ ማለት ግን ፖሊሲው ጫና የለውም ከፍ ሲልም መንገጫገጮችን አያስከትልም ማለት አይደለም። ይሁንና አስቀድሞ የተሸነፈ እንደሚባለው ከወዲሁ በፕሮፖጋንዳው ሰለባ መሆን ያልተፈለገ ዋጋን እንድንከፍል ሊያደርገን እንደሚችል ጠንቅቆ ሊገባን ይገባል፡፡

እዚህ ጋር ስለፖሊሲው እንቅልፍ አጥተን የጥፋት አቅሙን ብቻ ለማሳየት የሚታትሩት እነማን እንደሆኑ መገንዘብም ተገቢ ነው። የእነዚህ ግለሰቦች ፍላጎት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተለያይቶ እንዲያስብና ተግባብቶ እንዳይኖር መሆኑን፣ ፍላጎታቸውም የሚመኙትን ስልጣን ለመቆናጠጥ የሕዝብ ማሰቢያ ላይ የበላይነትና የበታችነት ወላፈን በመዝራት ስሜት በማነሳሳት ንዴት ማስታጠቅና እንዳሻቸው ሕዝቡን እየዘረፉ ሀብት ማከማቸት መሆኑን ጠንቅቆ ሊረዳ ይገባል።

ከሁሉም ቀድሞ ውሳኔው ይዞት የተነሳው ትልቅ ራዕይና አላማ በቅጡ መረዳት ይኖርብናል። ችኮላ አደገኛ መሆኑን መገንዘብና የምንፈልገው ነገር ዛሬውኑ ካልተደረገልን ሙግት ማስወገድ የግድ ይለናል። መልካም ውጤቱን «ዛሬና አሁኑኑ ካላየሁ» ከሚል ልጓም አልባ ስሜታዊነት ወጥተን፣ ገንቢ በሆነ ሂሳዊ አመለካከት «critical and constructive way of thinking»ን በማስቀደም የመነሻችን፣ የሂደታችንና የመዳረሻችን ምንነትና እንዴትነት በአግባቡ መረዳት ግድ ይላል።

ማንኛውም ትልም በተንጥል ጉዞ አይሳካም። የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብልጽግና የሚረጋገጠውም እንደ አንድ ነጋችን ታሳቢ በማድረግ በምንጽፈው ታሪክ፤ በምንወረውራት እያንዳንዷ ጠጠር ነው። እርስ በእርስ ትስስር፣ መተማመን፣ መግባባት ወንድማማችነት ከሁሉም በላይ የሀገር ባለቤትነት ስሜት ነው፡፡

ከተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ ሰዓት ሳንቆጥር፣ ድካማችንን ሳናስተዋል፣ ልዩነቶቻችን ለሀገር ልማት እንቅፋት ሳይሆን ካለፈው ታሪካችን ተምረን ለትውልድ የምወርሰው ስራ ለመሥራትና ለዚሁ የሚሆን መሠረት ለማስቀመጥ እጅ ለእጅ መያያዝ ይኖርብናል። ተመካክረንና ተደማምጠን ከሠራን፣ ተወያይተንና ተከራክረን ከተጓዝን፣ ተባብረንና ተጋግዘን፣ ተቻችለንና ተፈቃቅረን ወደፊት ከገሰገስን ኢትዮጵያን ከፈተና ወደ ልዕልና ከፍ ማድረግ ሙዝ የመላጥ ያህል ቀላል ይሆናል።

እስከዛሬ በመጣንበት መንገድ እየተባላን እየተናከስን በጎሳ እየተቧድንን ከተጓዝን ያው ጨለማ ውስጥ እንዳክራለን። ይህ እንዳይሆን ዙፋናዊ ጥማታቸውን ለማርካት ፀብን እየዘሩ ጥላቻን እያጎረሱ የሚኖሩ መንደርተኞች ልንታገላቸው ይገባል። ጨለማው እንዲቀጥል ፍላጎት እንዳላቸው በመረዳት የእኩይ ተልዕኮአቸው ማስፈፀሚያ እንዳንሆን ማስተዋልና ጥንቃቄን መታጠቅም ይኖርብናል፡፡

መንግሥትም መሰል የፖሊሲ ለውጦችን ሲያደርግ አስቀድሞም ሆነ በተግበራ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ በተለይም የሕዝብን ሥነ ልቦና የሚሰልቡ ፕሮፖጋንዳዎችን መከላከልና ፈጣንና በቂ መረጃን ተደራሽ ስለማድረግ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። ውሳኔን ተከትሎም ኢንቨስተሮች በስፋት እንዲገቡ ሰላምና መረጋጋት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ለነገ መባል የለበትም፡፡

በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው ከሕዝብ ደኅንነትና ከሀገር ህልውና የሚቀድም የለም። ሰላም በሌለበት ሁኔታ ትልልቅ ትልም ማለምም ማቀድ ፈታኝ ነው። ይህ እንደመሆኑም መንግሥት የዜጎች በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ በሰላም የመኖር፣ የመሥራትና የመንቀሳቀስ መብት በተጨባጭ ማረጋገጥ ግድ ይለዋል፡፡

ሰላም በአንድ ወገን ብቻ ስለተፈለገ የሚመጣ አይደለም። ሰላምን በሰለጠነ መንገድ ወንበር ስቦ በሃሳብ የበላይነት የሚገኝ ነው። የጠመንጃ ቃታ በመሳብ የሚገኝ ሰላም የለም፤ ኖሮም አያውቅ። በዚህ መንገድ ሰላምን ለማምጣት የሚደረግ የትኛውም ዓይነት ጥረት ትርፉ ኪሳራ ነው። የኪሳራው ዓይነት ደግሞ በማይተካ የሰው ሕይወትን ላይ የቆመ ነው፡፡

ሰላም በመፈለግ ብቻ አትመጣም፤ በተግባር መተርጎምና ቁርጠኛ መሆን ትፈልጋለች። ይህ እንደመሆኑም እንደ ሕዝቡም በዚህ ወቅት ለሀገር ሁለንተናዊ ግንባታ አቅም በሚሆን ሁናቴ ልዩነቶችን በመግራትና በማስተናገድ በአንድነት መቆም ይጠበቅብናል፡፡

መንግሥትም ሰላምን ከማረጋገጥ ባሻገር ፖሊሲው ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ እየተራመደ ስለመሆኑ በቅርብ ርቀት መከታተልና ለዚህም የሚሆን የማስፈጸም አቅም መገንባት ይኖርበታል። ይህ ካልሆነም በውሳኔው ጥቂቶች እንደፈለጉ የሚዘውሩት አደገኛ መሣሪያ የመሆን ዕድል ይኖረዋል። በመሆኑም መንግሥት የፖሊሲውን የትግበራ ሂደት አፈፃፀም በየጊዜው በመከታተል የተፈለገውን ውጤት አምጥቷል፣ አላመጣም፣ የሚለውን መገምገም ይኖርበታል። ከዚህም ከፍ ሲል ውጤቱ እየታየ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

በተለይም ከሰላም እና ጸጥታ ጋር ተያይዞ የሚነሱት ችግሮች ፈጣን እልባት መስጠት፣ ሎጂስቲክስና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት፣ በቋሚነት የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግና ከውስጥ ፍላጎት አልፎም የውጭ ምንዛሬ ማስገባት የሚያስችሉ ዋና ዋና ምርቶችን በስፋት በሀገር ውስጥ ማምረት ብሎም ለውጭ ገበያ ማቅረብ ታሳቢ ማድረግ ይገባል። በኢኮኖሚ የላቁ ሀገራት የከፍታቸው አብይ ምክንያት ውጤታማና ተጠያቂነት የሰፈነበት ተቋም መገንባታቸው ነው። ይህ እንደመሆኑ በኢትዮጵያ ለተቋማት ፈጠራና ሁለንተናዊ አቅም መጎልበት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የግድ ይላል፡፡

መገናኛ ብዙሃንም ውሳኔውን ሁለንተናዊ ፋይዳ አብዛኛው ማህበረሰብ በቀላሉ ሊረዳው በሚችል መልኩ ማስረዳትና ማስገንዘብ ይኖርባቸዋል። ከፋይዳው ባሻገር በትግበራ ሂደት ሊያጋጥሙ በሚችሉ መንገጫገጮችና ከፍ ሲልም አደጋዎች ማስገንዘብ አለባቸው። በዚህ ሂደት የሚያጋጥሙ ሕገወጦችን እንዲፋለም ማንቃትም እጅጉን ወሳኝ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ሕዝብም በአሁን ወቅትም በተለይም ኃላፊነት የማይሰማቸው ነጋዴዎች ምርት ያለ አግባብ በማከማቸትና እጥረት ያለ በማስመሰል የሚፈጥሩትን ኢኮኖሚያዊ አሻጥርና ምክንያት አልባ የዋጋ ንረት በማርገብ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርበታል። «መንስኤ ሳይሆን መፍትሔ» መሆን አለብን በሚል የፀና አቋም ተጠቃሚው ላልተፈለገ የዋጋ ንረት እንዳይጋለጥ ትልቅ አቅም መሆን አለበት፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## «ድንበር ተሻጋሪ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ኢትዮጵያን እንድናውቃት አድርጎናል»

በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች

**ክብረአብ በላቸው**

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሰው ልጅ ምንም ዓይነት ክፍያ የማያገኝበት ይበጃል፣ ይሆናል፣ ያስደስታልና የህሊና እርካታ ያስገኛል ብሎ ያለ ምንም ቀስቃሽና ጎትጓች በእራሱ ተነሳሽነት የሚፈጸም ተግባር ነው። የበጎ ፈቃድ ሥራ ማንኛውንም ዜጋ የሚያሳትፍ ቢሆንም በዋናነት ግን ወጣቶችን በስፋት የሚመለከት ይሆናል።

ማህበራዊ ትስስርን፣ አንድነትንና ፍቅርን የበለጠ እንዲጠናከር ማድረግ ማስቻሉ ደግሞ ሌላኛው የበጎ ፈቃድ ፋይዳ ነው። መንግሥታትን ከከፍተኛ የገንዘብ ወጪ በማዳን የሀገራትን ኢኮኖሚ ማጎልበትም ከሚሰጠው ጥቅም ጋር ይደመራል። በዚህ የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴ በበርካታ ሚሊዮን ብር ሊሰራ የማይችል ተግባር በየዓመቱ ሲከናወን ይስተዋላል፡፡

የበጎ አድራጎት ሥራ የእርስ በእርስ ትስስር አንድነት እንዲጎለብት ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪም የሚሰጠው ማህበራዊ መስተጋብር የጎላ ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት የተደራሽነት አድማሱን በማስፋት 21 ሚሊየን ወጣቶች እንዲሳተፉ ዝግጅት ስለማድረጉ የገለጸው የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚንስቴር በጎ ፈቃደኞቹ በ14 የሥምሪት መስኮች እንደሚሰማሩና በዚህም ከ52 ሚሊየን በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግ መታቀዱን ገልጾ ነበር።

የአረንጓዴ ዐሻራ፣ ደም ልገሳ፣ የአረጋውያንና አቅመ ደካሞች የቤት እድሳት፣ የትራፊክና የመንገድ ደኅንነት አገልግሎትና የማጠናከሪያ ትምህርት ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር (ዶ/ር) ዐቢይ አሕመድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ከግንዛቤ በማስገባት በተለይ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን፣ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ተማሪዎች እንዲሁም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በዚህ መልካም ተግባር እንዲሳተፉ ጥሪ ማቅረባቸው የሚታወስ እውነታ ነው። ከዚህ ጥሪ ጋር አያይዘውም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እስካሁን ድረስ የሚከናወነው ወጣቶቹ በሚኖርበት አካባቢ የተወሰነ ነው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ወጣቶቹ ወደ ሌሎች አጎራባች ክልሎች በመዘዋወር እግረ መንገዳቸውን አንድነታቸውንና የባሕል ዕሴቶቻቸውን የሚያጋሩበትና የሚያጎለብቱበት ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ቢሳተፉ መልካም ነው በማለት መልዕክት ማስተላለፋቸው ይታወሳል።

ይህንን የጠቅላይ ሚንስትሩን ሃሳብ መነሻ ያደረገው የ2016 ዓ.ም ወሰን ተሻጋሪ ወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አመራሮች በተገኙበት በጋሞ ዞን አርባ ምንጭ ከተማ ነበረ ጅማሮውን ያደረገው። የተለያዩ የሙያ ዘርፎችን ያካተተው የወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት "በጎነትና አብሮነት ለኢትዮጵያ ከፍታ" በሚል መሪ ሃሳብ የሁሉም ክልልና የሁለቱ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችን ተሳታፊ ያደረገ ነው።

ወጣት ሀብታሙ ብሩክ ከዘንድሮው የክረምት ወሰን ተሻጋሪ በጎ ፈቃደኞች መካከል አንዱ ነው። የመጣውም ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን ነው። በአካባቢያችን በተለያዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ ተሳትፎ እያደረግን የነበርን ወጣቶች ነን ወደዚህ የወሰን ተሻጋሪ በጎ ፈቃድ ሥራ የተጠራ ነው የሚለው ወጣት ሀብታሙ፤ በብዙ መልኩ ማህበረሰቡን ለመጥቀም ጥረት ያደረግንበት ነበር ይላል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ከአስራ ሁለቱም ክልልና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደር የተወጣጡ ወጣቶች ጋር በጋራ በመሆን ወደ ኦሮሚያ ክልል፣ ጋምቤላ ክልል፣ ሲዳማ ክልል፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ ሀረሪ ክልል፣ ሶማሌ ክልል፣ አፋር ክልል፣ ትግራይ ክልል፣ አማራ ክልል እና ድሬዳዋ ተጉዘናል የሚለው ወጣት ሀብታሙ በመጨረሻም አዲስ አበባን መዳረሻ ስለማድረጋቸው ይገልጻል።

ከዚህ በፊት በአካባቢያችን ከጓደኞቻችን ጋር እንጂ በዚህ መልኩ ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከተወጣጡ ወጣቶች ጋር የበጎ ፈቃድ ሥራ የመሥራት ዕድሉ አልነበረኝም የሚለው ወጣት ሀብታሙ፤ ይህ አጋጣሚ ኢትዮጵያን ለማወቅ እንደረዳቸው ተናግሯል።

የተለያዩ ባሕሎች፣ ወግ፣ ሥርዓት፣ አለባበስ ነበር እኛ ደግሞ ከመጣንበት አካባቢ ውጭ ያለውን የሌሎች ኢትዮጵያውያንን አኗኗር በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች በልዩነት ውስጥ ያለውን ውበት እና አንድነት እንድናውቅ እና እንድንረዳ መልካም አጋጣሚ ፈጥሮልናል


ወጣት ሀብታሙ


ወጣት ሙሉቀን

**የበጎ አድራጎት ሥራ የእርስ በእርስ ትስስር አንድነት እንዲጎለብት ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪም የሚሰጠው ማህበራዊ መስተጋብር የጎላ ነው**

ሲል ተነግሯል።

ወጣት ሀብታሙ እንደሚለው፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በባህሪው ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በጥብቅ የሚያቆራኝ እና የሚያስተሳስር ተግባር ነው። በመሆኑም በመማር ማስተማር፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ከተማ ግብርና፣ በደም እጦት ለሚሞቱ ለሚሰቃዩና ሕፃናትና ወላድ እናቶችን ለመታደግ የደም ልገሳ የተከናወነበት ነበረ ይላል።

"ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" እንደሚባለው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ወሰን ተሻጋሪ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች የአቅመ ደካሞችን ቤት በመሥራትና በመጠገን ለብርድ፣ ለዝናብ፣ ለአውሬ ለመሳሰሉት አደጋዎች እንዳይጋለጡ በማድረግ በስጋት ውስጥ ለሚኖሩት እፎይታን በመስጠት ድንቅ ተግባር አከናውነዋል የሚለው ወጣት ሀብታሙ፤ ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ወጣቶቹ "ሀገሬ ለእኔ ምን ሰራችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን ሰራሁላት" የሚለውን መርህ መፈክር በማድረግ ለሀገራቸው ያላቸውን ሀገራዊ ፍቅር ስለገለፁ ነው ብሏል።

ከወላይታ አካባቢ ቢመጣም ደሜን የሰጠሁት ጋምቤላ ክልል ነው የሚለው ወጣት ሀብታሙ፤ ስለዚህ የእኔ ደም ጋምቤላ ያለችውን እናት በደም ዕጥረት ከመሞት ታድጓታል፤ ይህ ማለት እንደ ሀገር አንድነታችንን ከማጉላት ባሻገር በደም የተሳሰርን ሕዝቦች መሆናችንን የሚያንፀባርቅ ነው ይላል።

«ሞት መልካም ሥራ እስከምንሰራ ድረስ አይጠብቃንም ስለዚህ መልካም ሥራ እየሰራን ሞትን እንጠብቅ» የሚለው ወጣት ሀብታሙ፤ እንዲህ እንዲል ያስገደደው ምን እንደሆነ ስናገር፤ በኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ ሰዎች መልካምነት ለማድረግ የሆነ ደረጃ ላይ እስኪደርሱ ይጠብቃሉ መኪና፣ ቤት፣ ብር ሲኖረኝ ከነገ ዛሬ በጎ አደርጋለሁ ብለው ያስባሉ። ይህ ትክክል አይደለም፤ ስለዚህ ነገ እንደሚሞት ሰው ካለን ጥቂት ነገር በማካፈል ነው በጎ ማድረግን መጀመር ያለብን ይላል።

በተለይ የዚህ የመልካም ተግባር ባለቤት የሆኑ ወጣቶች ኖሮኝ ወይም የሆነ ደረጃ ላይ ደርሼ መልካም ሥራ እሰራለሁ ከሚል አመለካከት ወጥተው የሚያከናውኑነው ማህበረሰብ ተኮር የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደመሆኑ ለጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ለአረጋውያን፣ ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች አቅማቸው በፈቀደ መጠን የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስልቶችን በመጠቀም እንደ ልብስ፣ ምግብና መሰል መሠረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላት ጀምሮ ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ እንደሚገባው ይናገራል።

ወጣት ሀብታሙ እንደሚነገረው፤ ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከመስጠታቸው በተጨማሪ በማህበራዊ ሚዲያ ድህረ ገጾች አማካኝነት ሰላም ጠፍቶ ግጭት፣ ልማት ጠፍቶ ጥፋት፣ እድገት ሳይሆን ውድቀት እንዲነግስ ለማድረግ ብሔርን ከብሔር፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት በማጋጨት የራሳቸውን ትርፍ ለማጋበስ የሚውተረተሩ ኃይሎችን አደብ ሊያስገዙ ይገባል ይላል።

ከግጭት፣ ከትርምስ ኪሳራ እንጂ ትርፍ እንደሌለው በአንክሮ መምከር እና ማስተካከል እንዲሁም በመረጃዎቹ ዙሪያ እውነተኛውን ነገር በማውጣት ማጋለጥ ከወጣቱ የሚጠበቅ ተግባር ነው የሚለው ወጣት ሀብታሙ፤ የተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ዛሬ እንደተመለከትኩት መሬት ላይ ያለው ፍቅር እና መተሳሰብ እንጂ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ እንዳለው ጥላቻ እና ፅንፈኝነት አይደለም ብሏል።

«ከሶማሌ፣ ከአፋር በአጠቃላይ ከሀገሪቱ አራቱም ማዕዘን ከመጡ ወጣቶች ጋር የመተዋወቅ እንዲሁም ጓደኝነት የመመስረት ብሎም ባሕላቸውን የማወቅና የእኔንም የማሳወቅ ዕድል አግኝቻለሁ» የሚለው ወጣት ሀብታሙ ይህ የእርስበርስ ግንኙነትን በማጠናከር የጋራችን ለሆነችው ኢትዮጵያ አንድነት የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ ነው ይላል።

ወጣት ሙሉቀን ታደገ ሌላኛው የወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተሳታፊና ከአማራ ክልል ዋግምራ ዞን ሰቆጣ ከተማ የመጣ ወጣት ነው እርሱ እንደሚናገረው፤ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች በመዞርበት ወቅት በጎ ተግባርን ከማድረግ ባለፈ ከሕዝቡ ጥሩ አቀባበልና ፍቅርን አግኝተናል ይላል።

በወሰን ተሻጋሪ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ማህበረሰብን እያገለገልን ቆይተናል የሚለው ወጣት ሙሉቀን፤ በሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ከተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ክልሎች ጋር ከመጡ ወጣቶች ጋር ሥራውን እየሰራን መቆየታችን የተለያዩ ልምዶችን እንድናገኝ ብሎም የጋራ አንድነት እንድንፈጥር ረድቶናል ይላል።

ኢትዮጵያ የተለያየ ቋንቋ የሚነገርባትና የተለያየ ባህል የሚንፀባረቅበት ሀገር ናት የሚለው ወጣት ሙሉቀን፤ ከዚህ አኳያ በወሰን ተሻጋሪ በጎ ፈቃድ ሥራ ከተወለድንበት አካባቢ ወጣ ብለን ያየነው በልዩነት ውስጥ አንድነት ያላት እንደ ሕዝብ በተለያዩ ጉዳዮች አመለካከታችን የተለያየ ቢሆንም ኢትዮጵያን በተመለከተ ግን የጋራ አቋም ያለን ሕዝቦች መሆናችንን ያረጋገጥኩበት ነው ይላል።

የአቅመ ደካማ ቤቶችን በመጠገን፣ ደም በመለገስ እንዲሁም ለተቸገሩ ወገኖች ከራሳችን ኪስ በመውጣት በዝቅተኛ ኑሮ ላይ የሚገኙ ዜጎችን የመደገፍ ሥራዎችን ሰርተናል የሚለው ወጣት ሙሉቀን፤ በተለይ በደም ልገሳ ፕሮግራሙ ሁሉም ወጣቶች ተሳታፊ ሆነዋል በዚህም ኢትዮጵያውያን በደም የተሳሰርን ዜጎች መሆናችንን ደግም ማረጋገጥ ችለናል ይላል።

ወጣት ሙሉቀን እንደሚናገረው፤ ወጣቱ በሚመለከተውና በማይመለከተው ጉዳይ ተጠምዶ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ነው ጊዜውን እያጠፋ ይገኛል። ይህ አካሄድ ደግሞ ለራሱ ለወጣቱ ብሎም ለሀገር ጉዳት እንጂ ጥቅም ይዞ አይመጣም። ስለዚህ በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚለቀቁና መርዘኛ የሆኑ ሃሳቦችን እየተመለከተና ለሌሎች በማጋራት ጊዜውን በከንቱ ከሚያባክን አንዲት የተቸገረች እናትን ባለው አቅም በመደገፍ የህሊና እርካታ ማግኘት ቢችል የተሻለ እንደሆነ ይናገራል።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የአንድ ጊዜ ተግባር ብቻ አይደለም የሚለው ወጣት ሙሉቀን፤ ወጣቶች ወደ መጡበት አካባቢ ሲመለሱ በጎ ተግባራቸውን በስፋት ሊተገብሩ ይገባል ይላል፤ በተለይም ወጣቶች በደረሱበት ቦታ ሁሉ ስለ ሰላምና ሕዝቦች አብሮነት በመሥራት ለሀገር ግንባታ በሚረዱ ጉዳዮች ላይ በአንድነት መቆም እንደሚያስፈልግ ይናገራል።

ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ይወዳደሉ፣ ይከባበራሉ ወይ የሚለውን በአካል የማየት አጋጣሚ መገኘቱ እንዳስደሰተው የሚናገረው ወጣት ሙሉቀን፤ «ኢትዮጵያውያን ዛሬም እንደሚዋደዱ በተግባር አይቻለሁ ከተለያየ አካባቢ ለመጣን ወጣቶች በኢትዮጵያዊነታችን ብቻ ፍቅር እና እንክብካቤ በሄድንበት አካባቢ ሁሉ አግኝተናል» ይላል።

ሙሉቀን እንደሚለው፤ ያለችን አንድ ሀገር ናት፤ በተለይ እንደ ወጣት ቁጭ ብለን በሕዝቦች መካከል ጥላቻ እና መቃቃርን ከመስበክ ይልቅ ያለንን አቅም ለበጎ ነገር በመጠቀም ሀገራችንን ከድህነት እና ኋላቀርነት ለመላቀቅ መትጋት መቻል አለብን ይላል። በተጨማሪም መንግሥት ከሀገሪቱ ሕዝብ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዘውን ወጣት በማስተባበር መሥራት ከቻለ ሀገሪቱን መለወጥ እንደሚቻል ይናገራል።

ሀገር ማለት ሰው እንደመሆኑ ሀገር የሚለውጥ መልካም ሃሳብ ያላቸው ግለሰቦች ሀገራቸውን ለማቅናት መንገድ ስለሚሆን በበጎ አድራጎት ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለባቸው የሚለው ሙሉቀን፤ የወጣትነት ትኩስ ጉልበት ለበጎነት ሲውል ደግሞ እንደ ሀገር ትርጉሙ ብዙ በመሆኑ በተለይ ወጣቶች በዚህ የክረምት የበጎ አድራጎት ሥራ በንቃት መሳተፍ እንደሚገባቸው ያስገነዝባል።

# የምድር በረከት

## «ኢትኖማይን»- የዲማ ወረዳው የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ኢትዮጵያ በወርቅ ማዕድን ክምችቷ ትታወቃለች። ቅርብ ጊዜ የወጣ መረጃ እንዳመለከተውም፤ በሀገሪቱ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት ከ517 ቶን በላይ የወርቅ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። ይህ የማዕድን ሀብት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የሚገኝ ቢሆንም፣ በትግራይ፣ በቤንሻንጉል ክልል፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች በስፋት እንዲለማ እየተደረገ ነው።

ይህ የወርቅ ማዕድን በአብዛኛው እየለማ ያለው ግን በባሕላዊ መንገድ ነው። የወርቅ ልማቱ በኋላ ቀር መንገድ እየተካሄደ ያለበት ሁኔታ አልሚዎችም ሆኑ ሀገሪቱ ከዚህ ማዕድን ሀብት ተገቢውን ጥቅም እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማዕድኑን የማውጣቱም ሆነ የግብይቱ ሥራ በሕገወጦች ቁጥጥር ስር እየሆነ ያለበት ሁኔታ ችግሩን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ አድርጎታል። ይህም ችግር ከወርቅ ማዕድን የሚገኘው ሀብት በአግባቡ እንዳይገኝ ተደርጓል። መንግሥት ይህን ሕገወጥ ተግባር ለመከላከልና ለመቆጣጠር ግብረ ኃይል አቋቁሞ እየሠራ ይገኛል።

ሕገወጥ ተግባሩን ከመከላከልና መቆጣጠር ጎን ለጎንም መንግሥት ሀገሪቱ ከወርቅ ማዕድኗ ምርት ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ መሥራቱን አጠናክሯል። ለእዚህም በባሕላዊ መንገድ የሚካሄደውን ወርቅ የማምረት ሥራ ለማዘመን፣ በባሕላዊ መንገድ የሚያመርቱትም ቢሆኑ በስፋት ወደ ልማቱ እንዲገቡ ለማድረግ እየሠራ ይገኛል። የወርቅ ልማቱ ማዕድኑ ባለባቸው ሌሎች ክልሎችና አካባቢዎች እንዲስፋፋ ለማድረግም ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።

በተለይ የወርቅ ልማቱን ለማዘመኑ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። ልማቱ በኩባንያ ደረጃ እንዲካሄድ ለማድረግ እየተከናወነ ባለው ሥራም በወርቅ ልማቱ የሚገኘውን ገቢ በብዙ እጥፍ ማሳደግ የሚያስችሉ ኩባንያዎች ወደ ዘርፉ ገብተው እንዲያለሙ እየተደረገ ነው። ይህን ተከትሎም አንድና ሁለት ብቻ የነበሩት የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች ቁጥር በቅርቡ እንደሚጨምር ይጠበቃል። አዳዲስ የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች በተለያዩ ክልሎች ላይ እየተገቡ ሲሆን፣ ግንባታቸውም በጥሩ ደረጃ ላይ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል «ኩርሙክ» እንዲሁም በጋምቤላ ክልል «ኢትኖማይን» የተሰኙ የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካዎች ግንባታ እየተካሄደ ያለበት ሁኔታም የወርቅ ማዕድን ልማቱን ለማዘመንና በኩባንያ ደረጃ ለማካሄድ ለተያዘው ጥረት ማሳያ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

በጋምቤላ ክልል ዲማ ወረዳ ተገኝተን የግንባታ ሥራውን የተመለከትነው የኢትኖማይን የወርቅ ፋብሪካ ሳይት ማናጀር ኢንጂነር ወልደገብርኤል አረጋዊ ክልሉ ትልቅ የወርቅ ሀብት ክምችት እንዳለው ይናገራሉ። ይህም በወርቅ ማዕድን ልማቱ ብዙ መሥራት እንደሚያስችልም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ፋብሪካው ልማቱን የሚያካሂደው በ16 ኪሎ ሜትር ስኩየር ቦታ ላይ ነው። ይህም ፋብሪካው ያረፈበት እና ወርቅ ፍለጋው የሚከናወንበት ስፍራን ያካተተ ነው ።

የማዕድን ጥሬ እቃ ወይም ወርቅ ያዘለ አለት የሚወጣበት ስፍራ በጣም ምቹ እና ትልቅ ሀብት ያለበት መሆኑን የሚገልፁት ኢንጂነር ወልደገብርኤል፤ በአሁኑ ወቅት የወርቅ ማዕድኑ የሚካሄድበት ፋብሪካ ግንባታ 90 ከመቶ በላይ ደርሷል ሲሉም አስታውቀዋል። የወርቅ አለት ያለበት ስፍራ የውስጥ ለውስጥ ግንባታም እየተከናወነ መሆኑን ተናግረው፣ ፋብሪካው ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ለመግባት ጫፍ ደርሷል ብለዋል።

በአካባቢው ያለው ወርቅ ያዘለ አለት በጣም ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ተፈላጊነቱም በዚያው ልክ መሆኑን ተናግረዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በአካባቢው ያለው ወርቅ በአንድ ቶን አፈር ውስጥ በአማካይ 22ነጥብ7 ግራም ወርቅ ይገኝበታል፤ የፋብሪካ በአካባቢው መገንባትም ይህን ሁሉ ታሳቢ ያደረገ ነው። ለዚህም የሚውል ለየት ያለ ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ ይውላል። የወርቅ ማዕድን አቅሙም ሆነ ያንን ለማውጣት የሚተከለው ፋብሪካ አቅም ለኩባንያው ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ ከፍተኛ ፋይዳ አለው።

በኢትዮጵያ የወርቅ ማዕድን በማውጣት ለመጠቀም የሚደረገው ጥረት እንደ ሀገር ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፤ ይህን ለመጠቀም ደግሞ ከቴክኖሎጂ፣ እውቀትና ሳይንሳዊ አሠራር በዘለለ ሰላም ወሳኝ ነው የሚሉት ኢንጂነሩ፣ ይህን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር በክልሉ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ክልል መዋቅር ድረስ መዘርጋቱንም ነው ያመለከቱት።

ኩባንያው ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ትልቅ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ በመሆኑ ለኩባንያው በነዋሪዎች ጭምር ጥበቃ ይደረግለታል ይላሉ። ክልሉም ሆነ የፌዴራል መንግሥት አስፈላጊውን የፀጥታ ሥራ እያከናወኑ እንደሚገኙ አስታውቀዋል፡፡

ፋብሪካው ለዜጎች የሥራ እድል እየፈጠረ መሆኑን ተናግረው፣ ግንባታው እየተካሄደ ባለበት በአሁኑ ወቅት ለ220 ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ፈጥሯል ሲሉም ጠቅሰዋል። ግንባታው ተጠናቆ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ሲገባ ደግሞ ከዚህ በላቀ ደረጃ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ጠቁመዋል።

የፋብሪካው የፕሮዳክሽን ሱፐር ቫይዘር አቶ ተስፋዬ ገብረ በበኩላቸው ኢትኖማይን የማዕድን ፋብሪካ ለኢትዮጵያ ትልቅ በረከት ይዞ መጥቷል ይላሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ ፋብሪካው በሰዓት 10 ቶን የወርቅ አፈር የሚፈጭ ሲሆን፣ በዓመት ደግሞ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ቶን አፈር ይፈጫል። በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር እስካሁን በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የማዕድን ፋብሪካዎች አዳዲስ ቴክሎጂዎችን የሚጠቀም ነው። አዲስ ቴክኖሎጂ የሚጠቀም በመሆኑም የአካባቢ ብክለት እና መሰል ተያያዥ ጥያቄዎችን አያስነሳም።

የአካባቢ ብክለትን እያስከተሉ ፣ ጥሩ ስም ሳይገነቡ ብሎም ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መልካም ግንኙነት ሳይፈጠሩ በመሥራት ዓለም አቀፍ ገበያ መውጣት አዳጋች መሆኑን ጠቅሰው፣ ዘመኑም የሶሻል ሚዲያ እና ኢንፎርሜሽን ዘመን ስለሆነ በተበላሸ አሠራር እና የአካባቢ ብክለትን በማስከተል ማምረት አይቻልም ብለዋል።

በአካባቢው ያለውን ትልቅ ፀጋ ለመጠቀም የሚደረገው ጥረት ማህበረሰብን ያማከለ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆን እንዳለበት ይታመናል ሲሉም አመልክተው፣ ኩባንያውም እነዚህን የደህንነት መርሆች በመከተል እንደሚሠራ ገልጸዋል። ወርቅ ለማግኘትና ለገበያ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት ወርቃማ አሠራሮችንም እንደሚከተል አስታውቀዋል።

አቶ ኡጁሉ ኦማኒ የዲማ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ናቸው። እሳቸው እንደተናገሩት፤ ወረዳው በከፍተኛ የማዕድን ሀብት ታድሏል፤ ሌሎች በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮችም አሉት። በአሁኑ ወቅት ወጣቶችን እና የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶች በሰፊው ወደ ሥራ እየገቡ ናቸው።

በወረዳው በማዕድን ዘርፍ ተስፋ ሰጪ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውንም አቶ ኡጁሉ ጠቅሰው፣ አካባቢው ወርቅ ልዩ መለያው መሆኑን አመልክተዋል። በወርቅ ማዕድን ላይ በሰፊው ጥናት መሰራቱንም ገልጸው፣ ለኮንስትራክሽን የሚውሉ በርካታ ማዕድናት በወረዳው እንዳሉም ጠቁመዋል።

ይህን ታሳቢ በማድረግ በርካቶች ፍቃድ አውጥተው እየሰሩ መሆናቸው ገልጸው፣ በአሁኑ ወቅት በወረዳዋ ሁለት ከፍተኛ አቅም ያላቸው ኩባንያዎች ፍቃድ አውጥተው በወርቅ ማዕድን ፍለጋ እና ማምረት ሥራ ላይ ተሰማርተው ትልቅ ለውጥ እያስመዘገቡ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በወረዳው በባሕላዊ መንገድ ወርቅ ፍለጋ ላይ የተሰማሩ አካላት የሚገኙ ሲሆን፤ ከእነዚህ ግዙፍ ፋብሪካዎች ጋር የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ሕጋዊ አሠራር፣ ድጋፍ እና ክትትል እየተደረገ ነው። በአካባቢው ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ቀድሞ ማስወገድና ሥጋት ለሚሆኑት ደግሞ ቀድሞ እልባት በመስጠትና ጥንቃቄ በማድረግ ሥራው እንዳይስተጓጎልም እየተሠራ ይገኛል። አካባቢው ለደቡብ ሱዳን ድንበር በቅርብ ርቀት የሚገኝ በመሆኑ ወረዳው፣ ዞኑ፣ ክልሉ እና የፌዴራል መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ ነው፡፡

በዲማ ወረዳ ብቻ በልዩ አነስተኛ የተሰማሩ ከ50 በላይ ፋብሪካዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ ዓለም አቀፍ ደረጃን ያሟሉት ፋብሪካዎች ሁለት ብቻ መሆናቸውን አስታውቀዋል። በአካባቢው ሀብት እና ጥናቶች ከሚያመላክቱት መረጃ አኳያ ግን ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው ሀብት ውስን ነው ሲሉ አመልክተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በልማቱ እየተከናወነ ባለው ተግባር በቂ ሀብት እየተገኘ ነው ማለት እንደማይቻል ጠቁመው፣ አካባቢው በወርቅ ሀብት ከፍተኛ አቅም ቢኖረውም በሕገ ወጥ የወርቅ ንግድ /ኮንትሮባንድ/ ሳቢያ ግብይቱ ፈታኝ እየሆነ መምጣቱን አስገንዝበዋል። ይህን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲያመች ሕጋዊ አሠራር መዘርጋት እንደሚገባ ገልጸዋል። ለእዚህም ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ፌዴራል መንግሥት የተጠናከረ ሥርዓት መዘርጋት ብሎም ከአጎራባች ሀገራት ጋር መነጋገርና መስማማት ይገባል ብለዋል። በብሔራዊ ባንክ በኩልም በወርቅ ግብይት ላይ ያለውን አሠራር በማጤን ጥቁር ገበያ የሚቆመበትን ሁኔታ ለመፍጠር በተጠናከረ መንገድ መሥራት እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

የጋምቤላ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ኡመድ ኡጁሉ በበኩላቸው፤ ማዕድን በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋና የዕድገት ተኮር ዘርፍ ተብለው ከተለዩት አምስት ዘርፎች አንዱ መሆኑን አመልክተዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በክልሉ የተለያዩ የማዕድን ሀብት ክምችቶች እንዳሉ ይታወቃል። በዋናነት የወርቅ ማዕድን በስፋት የሚገኝ ሲሆን፣ በክልሉ አራት ወረዳዎች (አኙዋሃ ዞን ዲማ፣ አቦቦና ጋምቤላ ወረዳዎች፤ ማጃንግ ዞን መንገሺ ወረዳ) የወርቅ ማዕድን ክምችት ይገኛል።

በዚሁ መሠረት በወርቅ ምርት እስካሁን ለብሔራዊ ባንክ ገቢ የተደረገ የወርቅ መጠን አስመልክተው ሲያብራሩ እንደገለጹት፤ 2011 በጀት ዓመት 122ነጥብ24 ኪሎ ግራም፣ በ2012 በጀት ዓመት 264ነጥብ24 ኪሎ ግራም እንዲሁም በ2013 በጀት ዓመት 1212 ነጥብ 24 ኪሎ ግራም ወርቅ ገቢ ሆኗል። በ2014 በጀት ዓመት ደግሞ 1206 ነጥብ51 ኪሎ ግራም ፣ በ2015 ዓ.ም 236 ኪሎ ግራም ወርቅ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ብቻ 225 ኪሎ ግራም ወርቅ ገቢ ተደርጓል። የሚመረተውም የወርቅ ምርት በየወቅቱ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ በማድረግ ክልሉ ለሀገር ልማት የበኩሉን ድርሻ እያበረከተ ይገኛል፡፡

የወርቅ ሀብት በአግባቡ በማልማት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጥቅም እንዲውል ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል። ባሕላዊና አነስተኛ ወርቅ አምራቾች ቁጠባን መሠረት በማድረግና ዘመናዊ ማምረቻ መሣሪያዎችን በመጠቀም እንዲያመርቱ በማድረግ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግም እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኘውን የወርቅ ማዕድን ለመጠቀም ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም፣ ሀገሪቱ ያላትን የማዕድን እምቅ ሀብት በመጠቀም ረገድ ብዙ ርቀት መጓዝ እንዳለባት የዓለም ባንክ መረጃም ይጠቁማል። በተለይም አሳማኝና በቂ የማስተዋወቅ ሥራ አለመሠራቱ፣ ጊዜ ቆጣቢና ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የማዕድን አወጣጥ ፍቃድ አሰጣጥ ሥርዓት አለመዳበር፣ በዘርፉ በበቂ ደረጃ የሰለጠኑ ባለሙያዎች አለመኖር፣ ከመሬት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ግጭቶች ከወርቅ ልማቱ ፈተናዎች መካከል ይጠቀሳሉ።



**የወርቅ ማምረቻ ፋብሪካው ግንባታ አፈፃፀም ከ90 በመቶ በላይ ደርሷል**

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ከልጅነት ድርሳን..

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አሎምፒክ ቁርስ ቤት ሠፈራችን አስፓልቱን ተሻግሮ ያለ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የተቀባ ብቸኛው ቁርስ ቤት ነው። የቁርስ ቤቱ ባለቤት አቶ አብዱቃድር ሁሴን ይባላሉ። ሰፈር ውስጥ ማንም አብዱቃድር ብሎ የሚጠራቸው የለም። ጋሽ አብዲ ነው የሚላቸው። በረጅም ጢም ያጌጠ ጠይም ሩህሩህ ፊት አላቸው። ጉንጫቸው ዘወትር በጫት ተጎስሮ እንዳረገዘ ነው። ከወገባቸው ላይ ሸርጥ፣ ከብብታቸው ስር ጫት አይጠፋም። እግራቸው ሁሌም በነጠላ ጫማ ነው። የልጅነቴ ትልቁ ትዝታዬ ጋሽ አብዲና አሎምፒክ ቁርስ ቤት ነው። ጠዋት ማልጄም ሆነ ከሰአት አርፍጄ ወዳሉበት ስሄድ የሚሰማኝ ደስታ ልኬት የለውም። በልጅነቴ አሎምፒክ የሚለውን ቃል ለማንበብም ሆነ ለመጥራት እንገዳገድ ነበር። ከሠፈራችን ከናሆም በቀር አሎምፒክ የሚለውን ቃል በትክክል የሚጠራ እኩያ አልነበረኝም። አብዛኛው የሰፈር ልጅ የጋሽ አብዲን የቁርስ ቤት ስም በመጥራት ነበር ጉብዝናውን የሚለካው። አንድም ቀን ግን ሳንሳሳት ጠርተነው አናውቅም ነበር፡፡

በልጅነቴ ጋሽ አብዲ ስላሉበት ብቻ ሠፈራችን ገነትን ይመስለኝ ነበር። ቁርስ ቤቱ ሰማይ ቤት ጋሽ አብዲ ደግሞ እግዜርን ይመስሉኝ ነበር። እናቴ ዛሬም ድረስ ያልበላሁትን ጣት የሚያስቆረጥም ቁርስ ሠርታልኝ እንኳን የጋሽ አብዲን አሳንቡሳና ጭርናቄ ያክል አይጣፍጠኝም ነበር። እናቴ ብስኩት እንዳልበላ ያልነገረችኝ ተረት የለም። ዘይት ሆድ ያማል፣ ከትምህርት ሰነፍ ያደርጋል እያለች አሳንቡሳና ጭርናቄ እንድሸሽ የለፋች ቢሆንም አልተሳካላትም። ዞሬ ዞሬ መገኛዬ ጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት ጋ ሆነ። ፈልጋ የምታገኝኝ በር ላይ ቆሜ በበላተኛ ርካታ ምራቄን ስውጥ ሆነ። ከጭርናቄ ፍቅር የተነሳ እናቴን ትምህርት ቤት ሄድኩ እያልኩ ውሎዬ እዛ ነበር፡፡

በልጅነቴ እንደ እኛ ሰፈር ልጅ የሚበዛበት ሰፈር አልነበረም። የሆነ ደመነፍስ አለን መለሰኝ የሰፈር ልጆች ሁሉ ሳናውቀው መገኛችን ጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት በር ላይ ነበር። የጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት ከዳቦና ሻይ ባለፈ ብቸኛው ቴሌቪዥን ያለበት ቤትም ስለነበር ከዛ ቤት አንጠፋም። በልጅነታችን ሃይሌንና ቀነኒሳን፣ ደራርቱንና ጡርዬን የተዋወቅናቸው እዛ ቤት ነው። ልጅነቴ ያለቀው እዛ ጭርናቄ ቤት ነው ብል አበልኩ አልልም። አይ ጋሽ አብዲ..ለዛ ሁሉ የሰፈር ልጅ የሚሆን ደግነት ነበራቸው። ጋሽ አብዲ በር ላይ ቆሞ አሳንቡሳና ጭርናቄ ሳይበላ ቤቱ የሚገባ ልጅ አልነበረም። ከደግነታቸው የተነሳ ቁርስ ቤቱን የከፈቱት ድሆችን በነጻ ለመመገብ ይመስለን ነበር። ዛሬ ነው ጋሽ አብዲ ለዛ ሁሉ ለሰፈራችን ድሃ ማህበረሰብ የእግዜርን ያክል ዋጋ ያላቸው አባት እንደሆኑ የገባኝ። አድጌ ያን የልጅነት ሰፈሬን እስከለቀኩበት ጊዜ ድረስ እናቴ እጄን አንጠልጥላ ወደ ቤት የምትወስደኝ ከጋሽ አብዴ ቁርስ ቤት በር ላይ ነበር፡፡

ማልጄ ወይም አርፍጄ ብቻ በቀናኝ በአንዴ ጭርናቄ ቤቱ በር ላይ ሆኜ እቀላውጣለሁ። ጋሽ አብዲ እስኪያዩኝ ድረስ ወዲያ ወዲህ እላለሁ..እንዲያም ሆኜ አላይ ካሉኝ ጉንፉን ያለብኝ መስዬ እስላለው እንዲያም ብዬ አልሰማ ካሉኝ ወደ ውስጥ ገብቼ ያልጠማኝን በባዶ ሆዴ ውሃ እጠጣለሁ። ይሄ ሁሉ በዛ በልጅነቴ ጠዋት ውስጥ ጋሽ አብዲ እንዲያዩኝ የምከፍለው መስዋዕት ነበር። አዩኝ ማለት ወይ ጭርናቄ ወይም ሳምቡሳ ይሰጡኛል። ጋሽ አብዲ አይተውኝ ዝም ያሉኝ ጊዜ የለም። እንዳዩኝ ‹አንተ ትምህርት እንዴት ነው? አባትህ ተሻለው እንዴ? እናትህስ እንዴት ናት..እቁቡን ምነው ተወችው? አንዱንም ሳልመልስላቸው ሰላሳ ጥያቄ ይጠይቁኛል። ደስ የሚለው ነገር ጋሽ አብዲ ጥያቄ ጠይቀው መልስ አይፈልጉም። የነጻነቴ ስፍራ ናቸው። አባዬ እንደሳቸው ቢሆን ስል እመኝ ነበር። አባዬ ጥያቄ ጠይቆኝ መልስ ሳይጠብቅ ቀርቶ አያውቅም። ጥያቄዎች ሁሉ መልስ አላቸው ብሎ የሚያስብ ሞገደኛ አባት ነው። አንዳንድ ጊዜ ጠይቆኝ ካልመለስኩለት ንቀት ወይም ደግሞ ትዕቢት ይመስለውና መኻታው በላይ በሰቀላት አለንጋው ይጀልጠኛል። ጋሽ አብዲ እንዲህ አይደሉም..ከጥያቄ በኋላ እጃቸው ሳይዘረጋልኝ ቀርቶ አያውቅም። አባቴ ጠይቆኝ ዝም ካልኩ በአለንጋ ነው የሚጀልጠኝ ጋሽ አብዲ ደግሞ ጭርናቄ ነው የሚሰጡኝ። ‹ማነው የሚወደኝ አባቴ ነው ወይስ ጋሽ አብዲ? ስል አስባለሁ። በልጅነቴ አባቴን በጋሽ አብዲ ልለውጠው ትንሽ ነበር የቀረኝ። ቶሎ ባላድግና ሰፈር ባንቀይር ኖሮ አባቴ ጋሽ አብዲ ናቸው ስል አዋጅ አስነግር ነበር፡፡

በልጅነቴ ብዙ ጭርናቄ ለመብላት የጋሽ አብዲ ልጅ መሆን ያጓጓኝ ነበር። አጠገባቸው ምንጣፋቸው ቁጭ ብዬ የሚሆኑትን መሆን፣ የሚያደርጉትን ማድረግ ይናፍቀኝ ነበር። በልጅነቴ ተመኝቼ ያጣሁት ወይም ደግሞ ቀረብኝ ብዬ የምቆጭበት የጋሽ አብዲ ልጅ ሆኜ አለመፈጠሬ ነበር። አቤት ብስኩት ስወድ..አቤት ጭርናቄ ስወድ። አንዳንድ ጓደኞቼ ዶክተር ወታደር ሲሉ ግን ሳድግ እንደ ጋሽ አብዲ ጭርናቄ ቤት ከፍቼ ለመኖር ነበር የምመኘው። የጋሽ አብዲ ቁርስ ቤት ልጅነቴ ተጀምሮ ያለቀበት ሥፍራ ነው። መሸቶ የሚነጋልኝ እዛ ነበር። ሁልጊዜ ጠዋት ወደዛ ስሄድ አሳምቡሳው፣ ጭርናቄው ብረት በሚመስል ነገር ላይ በላስቲክ ተሸፍኖ ሳይ ከየት እንደመጣ የማላውቀው የምራቅ ጎርፍ አፌ ውስጥ ይጎርፍ ነበር። እንዴትና ከየት እንደሚያመጡት አላውቅም። ሲጠበስ ለማየት፣ ቆሜ ለመቀላወጥ ያላደረኩት ጥረት የለም። ግን ጠዋት ደጅ ላይ ስቆም ብስኩቱ ተጠብሶ ነው የማገኘው። ዛሬም ድረስ ባልነቃሁት ጠዋት ከነ አይናሬና ከነልጋጌ ነቅቼ ወደ ጋሽ አብዲ ቤት ስሄድ ሸርጣቸውን አገልድመው፣ ጫታቸውን ብብታቸው ስር ወሽቀው በላተኛ ሲያስተናግዱ አያለሁ። ያኔ ብዙ ሃሳቦች ይመላለሱብኛል። መቼና እንዴት እንደነቁ አላውቅ እላለሁ። በዛ ለሊት በነቃና በበቃ ሰውነት ሳያቸው አስቤ አልደርስባቸውም። በዛ ውድቅት ለሊት እሳቸውን ሳይ እኛ ብቻ የምንተኛ ይመስለኛል። በዛ ለሊት ካልተኙ መች ተኝተው ነቁ? ያ ለሊት እኮ የመተኛ ለሊት ነበር.. እማዬና አባዬ እንኳን አልነቁም። ጠዋት.. በጣም ጠዋት ማልደው በመነሳት ጸሎት የሚያደርሱት የእማዬ አባት እንኳን ለጸሎት አልተነሱም። ጋሽ አብዲ እንዴት ተነሱ? ተኝተው የማያድሩ ሰው ናቸው ስል ደመደምኩ፡፡

ልጅነቴ አልቆ ጎለመስኩ..ነፍስ ሳላውቅ፣ ጋሽ አብዲንም ሆነ ጭርናቄ ቤታቸውን ሳልጠግብ ሀገር ቀየርን። ከብዙ ዓመት በኋላ ወደዛ ሰፈር ተመለስኩ። እውነት ለመናገር ጋሽ አብዲን አግኝቶ እንደ ማመስገንና ትናንትን አስታውሶ እንደማውጋት ምኞት አልነበረኝም። በልጅነቴ ውስጥ ያስቀመጡት ብዙ፣ እልፍ የራሮትና የደግነት ውለታ አለ። ያን ውለታ የምመልስበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ስለነበርኩ ላገኛቸው ቸኩያለው። በልጅነቴ የማውቃቸው ጓደኞቼ እንኳን የጋሽ አብዲን ያክል አልናፈቁኝም፡፡

ወደ ልጅነት ሰፈሬ ደርሼ ወደጭርናቄ ቤቱ አመራሁ። ያ የማውቀው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የተቀባው ጭርናቄ ቤት አልነበረም። ትልቅ ሆቴል ተገንብቶበታል። በሆቴሉ ግራና ቀኝ የተለያዩ ዘመናዊ ስቆች አሸብርቀውበታል። ወደ ውስጥ ገብቼ ስለጋሽ አብዲ ለመጠየቅ ወደ አንድ አስተናጋጅ ስንደረደር.. በቅርብ ርቀት ላይ የሚያምር ሶፋ ላይ አንድ አዛውንት ተመለከትኩ። ሸርጥ ያሸረጡ፣ ረጅም ጢማቸው ቀይ ቀለም የተቀባ አዛውንት። ባለሁበት ቆምኩ ጋሽ አብዲ ስለመሆናቸው ቅንጣት ጥርጥር አልነበረኝም። እውነት እንባዬ መጣ..ሳያቸው እነዛ መስጠት የማይሰለቻቸው ደግ እጆቻቸው፣ ያቺ ለድሃ የማይቸግራት ነፍሳቸው ፊቴ ላይ አንጃበቡ። አስተናጋጁን ትቼ ወደእሳቸው ተራመድኩ። አጠገባቸው መመርኮዣ ምርኩዝ አየሁ፡፡

አጠገባቸው ደርሼ ‹ጋሽ አብዲ? አልኳቸው። አልሰሙኝም..

ወደ ፊቴ ጎንበስ ብዬ ‹ጋሽ አብዲ? ስል ደገምኩላቸውሁ።

ቀና ብለው አዩኝ። ያስታወሱኝ አይመስለኝም። ሁለት እጄን ሰድጄ እጃቸውን ጨበጥኳቸው። በዛ አላበቃሁም እጆቻቸውን ደጋግሜ ሳምኳቸው። በዚህም አላበቃሁም በእየሱስ እግር ላይ እንደተደፋችው መቅደላዊት ማርያም እጆቻቸው ላይ ተደፍቼ በእንባዬ አጠብኳቸው። ይሄ ሁሉ ሲሆን ምንም አላሉኝም፡፡

ከሲቃዬ ጋር እየታገልኩ ‹አቡሌ ነኝ! አልኳቸው፡፡

አላስታወሱኝም..ቢያስታውሱኝ እንዴት መልካም ነበር። የነፍሴን ብዙ አመት፣ የታሪኬን እልፍ ንጋት መልሼ ማን እንደሆንኩ ላስታውሳቸው ሞከርኩ። ድሮ ከድህነታቸው ላይ ቆርሰው በነጻ የሚሰጡኝን እነዛን መቼም ያልበላኋቸውን ጣፋጭ ጭርናቄዎች አስታውሼ ማን እንደሆንኩ ነገርኳቸው አላስታወሱኝም፡፡

ሰው ደግ ልብ ሲኖረው እንዲህ ነው.. ያደረገውንም የተደረገበትንም አያስታውስም፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የቬንዝዌላው ፕሬዚዳንት ማዱሮ እና ቢሊየነሩ ኢለን መስክ ሊደባደቡ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቬንዝዌላው ፕሬዚዳንት ኒኮላስ ማዱሮ እና ቢሊየነሩ ኢለን መስክ ለመደባደብ መስማማታቸው ተነገረ፡፡

ባለፉት ጊዜያት በማህበራዊ ትስስር ገጽ እና በመገናኛ ብዙሃን ሃይለ ቃላትን ሲለዋወጡ የሰነበቱት ሁለቱ አካላት ንግግራቸውን በድብድብ ለመደምደም ተስማምተዋል፡፡

ኒኮላስ ማዱሮ ባሰለፍነው እሁድ ለሶስተኛ ጊዜ የሥልጣን ዘመን ማሸነፋቸው ይፋ መደረጉን ተከትሎ በኤክስ ገጹ ላይ “አጭበርባሪ ፕሬዚዳንት” በሚል የገለጻቸው መስክ በሥልጣን መቀጠል የሌለባቸው ፕሬዚዳንት ሲል ወርፏቸዋል፡፡

ቀጥሎም የቬንዝዌላ ዜጎች የማዱሮን ሀውልት አፍርሰው የቀድሞውን የሀገሪቱን ፕሬዚደንት ሁጎ ቻቬዝ ሀውልት ሲተክሉ የሚያሳይ የተቀነባበረ ተንቀሳቃሽ ምስል በገጹ ላይ ለጥፏል፡፡

ፕሬዚዳንቱ መስክ በደቡብ አሜሪካዊቷ ሀገር አመጽ እና ብጥብጥን የመፈጥር ዓላማ ያለው ሀገራችንንም በስፔስ ሮኬቶቹ መውረር የሚፈልግ ዋነኛ ጠላታችን ነው ሲሉ ከሰሰውታል፡፡

ማዱሮ ሰኞ እለት በሀገሪቱ ብሄራዊ ቴሌቪዥን ቀርበው “ከኔ ጋር መጣላት ትፈልጋለህ ቦታ እና ጊዜውን መርጠህ አሳውቀኝ እኔ የቻቬዝ እና ቦሊቫር ልጅ ነኝ” ሲሉ ዝተዋል፡፡

ይህን ተከትሎ የፕሬዚዳንቱን የይዋጣልን ጥያቄ መቀበሉን ያስታወቀው መስክ እኔ ካሸነፍኩ ማዱሮ ከሥልጣን ላይ ይወርዳሉ ከተሸነፍኩ ደግሞ ፕሬዚዳንቱን በነጻ ወደ ማርስ የሽርሽር ጎዞ እጋብዛቸዋለሁ ብሏል፡፡

የስፔስ ኤክስ እና ቴስላ ዋና ስራ አስፈጻሚው ቢሊየነሩ ኢለን መስክ የተለያዩ ታዋቂ እና ተጽኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን በመወረፍ እና ቡጢ ቢውዳደሩ እንደሚያሸንፉቸው በመፎከር ይታወቃል፡፡

ከዚህ ቀደም የፌስቡክን መስራች ማርክ ዙክርብርግ የቡጢ ውድድር ይዘጋጅልን እና እንተያይ የሚል ጥቄ አቅርቦ እንደነበር ይታወሳል፡፡

አሁን ላይ ደግሞ ከቬንዝዌላው ፕሬዚዳንት ጋር ተፋጥጠዋል፡፡ ሁለቱ አካላት እንዳሉት ፊት ለፊት ለመቧቀስ ይገናኛሉ ተብሎ አይጠበቅም ሆኖም ማዱሮ የሀገር መሪ ሆነው የእንቧቀስ ጥያቄ ማቅረባቸው መነጋገርያ ሆኗል፡፡





የቬንዝዌላ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ኒኮላስ ማዱሮ 51 በመቶ የመራጮችን ድምጽ በማግኘት ሀገሪቱን ለሶስተኛ ተከታታይ የሥልጣን ዘመን ማስተዳደር የሚችሉበትን ይሁንታ ማግኘታቸውን አስታውቋል፡፡

ይህን ተከትሎም ከሰኞ ጀምሮ ምርጫ ተጭበርብሯል ያሉ የሀገሪቱ ዜጎች በአደባባይ ተቃዎሚቸውን እየገለጹ ይገኛሉ፡፡




## ፌስቡክ እና ኢንስታግራም በሶስት ወራት ውስጥ 39 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አገኙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፌስቡክ እና ኢንስታግራም በሶስት ወራት ውስጥ 39 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አገኙ።

የሜታ ኩባንያ ንብረቶች የሆኑት ፌስቡክ እና ኢንስታግራም ባለፉት ሶስት ወራት ከፍተኛ ገቢ ማግኘታቸውን አስታውቀዋል።

ኢንስታግራም እና ፌስቡክ ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ 39 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘታቸውን አስታውቀዋል።

ሁለቱ ኩባንያዎች ያገኙት ገቢ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ13 ቢሊዮን ዶላር ወይም የ20 በመቶ ብልጫ አለው ተብሏል።

ኩባንያዎቹ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መጠቀማቸው ለገቢያቸው መጨመር ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ተገልጿል።

በዓለማችን ካሉ የማህበራዊ ትስስር ገጾች መካከል ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑት ፌስቡክ እና ኢንስታግራም በሜታ ኩባንያ ስር ካሉ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች መካከል ዋነኞቹ ናቸው።

የድርጅቱ መሥራች እና ባለቤት ማርክ ዙከርበርግ እንዳስታወቀው ተወዳዳሪ ለመሆን እና ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት እንዲረዳቸው በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ 40 ቢሊዮን ዶላር ወጪ እንደሚያደርጉ አስታውቋል።

መሠረታቸውን አሜሪካ ያደረጉት ሜታ፣ ጎግል እና ማይክሮሶፍት ኩባንያዎች የተሻሻለ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መተግበሪያ ለመሥራት ፉክክር ላይ ናቸው።

70 ሺህ ሠራተኞች ያሉት ሜታ ኩባንያ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ አማካኝነት ሠራተኞችን እየቀነሰ ይገኛል።

ድርጅቱ በፈረንጆቹ 2022 ላይ በመላው ዓለም ላይ 80 ሺህ ሠራተኞች ነበሩት።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

## ስፖርትን ለታላቅ የበጎ አድራጎት ሥራ የተጠቀመ ተቋም

**አንተነህ ቸሬ**

ዓለም የተራቀቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በየቀኑ እየተመለከተች ባለችበት በዚህ ዘመን፣ መከራዋና ሰቆቃዋም እየበዛ ነው። በየቦታው የሚፈጠሩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች ሕዝቦቿን ለስቃይና መከራ መዳረጋቸውን ቀጥለዋል። እነዚህ ችግሮች ከሚፈጥሯቸው ማኅበራዊ ቀውሶች መካከል አንዱ የጎዳና ተዳዳሪነት ነው። የጎዳና ተዳዳሪነት በኢትዮጵያም ተንሰራፍቶ የሚታይ ማኅበራዊ ቀውስ ነው። በኢትዮጵያ በ11 ዋና ዋና ከተሞች ከ89ሺ በላይ ጎዳና ተዳዳሪዎች እንዳሉና ከእነዚህም ውስጥ ከ55ሺ በላይ የሚሆኑት በአዲስ አበባ እንደሚገኙ ከአራት ዓመታት በፊት ይፋ የተደረገ መረጃ ያሳያል፡፡

ችግሩን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችም ስር ነቀል ለውጥ ማስመዝገብ አልቻሉም። በችግሩ ምክንያት የሚፈጠሩ ቀውሶች ቤተሰብን፣ ህብረተሰብንና ሀገርን ብዙ ዋጋ እያስከፈሉ ነው። ይህ አደገኛ ችግር ያሳሰባቸው በጎ አሳቢ ዜጎች፣ ችግሩ ከዚህ የበለጠ ቀውስ እንዳያስከትል በየጊዜው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ ይስተዋላል። የበጎ አድራጎት ተቋማትን በማቋቋም የሚከናወኑ ምግባረ ሰናይ ተግባራት ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

በኢትዮጵያ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ምግባረ ሰናይ ዓላማዎችን አንግበው የተቋቋሙና የሚንቀሳቀሱ በርካታ የበጎ አድራጎት ተቋማት አሉ። እነዚህ ተቋማት የተቸገሩ ወገኖች ድጋፎችን እንዲያገኙ በማድረግ ድጋፍ የተደረገላቸው ዜጎች የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው በማስቻል ሞራልና ማኅበራዊ ፍትሕ የሰፈነበት ማኅበረሰብና ሀገር ለመገንባት ቀላል የማይባል ሚና ይጫወታሉ።

እነዚህ የበጎ አድራጎት ተቋማት በተለያዩ መንገዶች የሚመሰረቱ ሲሆን፣ ዓላማቸው በተለያዩ ምክንያቶች የተቸገሩ ወገኖችን በማገዝ ከችግሮቻቸው እንዲላቀቁ መርዳት ነው። ለአብነት ያህል ለስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የተሰባሰቡ ግለሰቦች በስፖርት አካልንና አዕምሮን ለመገንባት ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ስፖርታዊ መሰባሰባቸውን የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት ሲጠቀሙበትም ይስተዋላል። በዚህ መንገድ ተመስርተው የብዙ ዜጎችን ሕይወት የታደጉ በጎ ተግባራትን የሚያከናውኑ የበጎ አድራጎት ተቋማት አሉ።

ከእነዚህ ተቋማት መካከል አንዱ ከአምስት ዓመታት በፊት የተመሰረተው ‹‹ጳጉሜን አምስት (፭)›› የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። የ‹‹ጳጉሜን አምስት (፭)›› የበጎ አድራጎት ድርጅት መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ ማስተር ኤርሚያስ ገሰሰ እንደሚገልፁት፣ ድርጅቱ ሕጋዊ እውቅናና ፈቃድ ያገኘው በ2011 ዓ.ም ቢሆንም፣ እሳቸው የበጎ አድራጎት ሥራ መሥራት የጀመሩት ግን የማርሻል አርት ስልጠና መስጠት ከጀመሩበት ከ1995 ዓ.ም አንስቶ ነው።

ሥራውን እንዲጀምሩ ካነሳሷቸው ምክንያቶች አንዱ እሳቸው ያጠኑት የስፖርት ዓይነት፣ ከማርሻል አርት ጥበቦች መካከል አንዱ የሆነው፣ ጅት ኩን ዶ (Jeet Kune Do) እንደሆነ ይገልፃሉ። ‹‹ይህ የማርሻል አርት ክዋኔ ተፈጥሯዊ ጥበብን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል (ራስን ማወቅ፣ መግለፅና መሆን) የሚያስተምር ነው ይላሉ።

‹‹እነዚህን ነገሮች የተገነዘበና የተረዳ ሰው ከራሱ አልፎ ለራሱና ለሌላው ዜጋ ያስባል። እኔ የማስተምረው የተማሪ ስብስብ ብዛትና ያለው አቅም ከፍተኛ ነው። ይህን ስብስብ አዎንታዊ በሆነ መልኩ እንዴት ለሀገር ጥቅም ማዋል በሚቻልበት ላይ አሰብኩ። ከሕፃናት እስከ አዋቂዎች ብዙ ተማሪዎች ስለነበሩ ተማሪዎቹን በማሰባሰብ ይህን ኃይል ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ማድረግ ወሳኝ ተግባር ነበር። ስብስቡ ጉልበት፣ እውቀትና ሙያ ያለው በመሆኑ ምን ብናደርግ ነው ለሀገር ጥቅም ልናውለው የምንችለው ብዬ አስብ ነበር።

ጎዳና ላይ የሚኖሩት ወገኖች እጅግ አሳዛኝ በሆነ ሕይወት ውስጥ ነበሩ። በየዕለቱ በጎዳናዎች ላይ የምናያቸው ጎዳና ተዳዳሪዎች የብዙ ችግሮቻችን መገለጫዎች ናቸው። የጎዳና ተዳዳሪዎቹን ከስፖርቱ ሰልጣኞች ጋር በማቀናጀትና ድጋፍ በማድረግ ከችግራቸው ማውጣት እንደሚቻልም አመንኩ። ይህን ሃሳብ ለሰልጣኞቹ ሳቀርብላቸው ሰልጣኞቹ ሃሳቤን በደስታ ተቀበሉት። ወቅቱ የትንሳዔ በዓል የደረሰበት ጊዜ ስለነበር፣ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ለጎዳና ተዳዳሪዎች ድጋፍ በማድረግ የበጎ አድራጎት ሥራውን ጀመርን›› በማለት ስለበጎ አድራጎት ሥራቸው አጀማመር ያስታውሳሉ።

ስለድርጅቱ ስያሜ ሲስረዱ ደግሞ፣ ‹‹ጳጉሜን በአዲሱና በአሮጌው ዓመት መካከል የምትገኝ ድልድይና የተስፋ ወር ናት። ከዚህ በተጨማሪም ጳጉሜን ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ብቸኛዋ የ13 ወራት ፀጋ ባለቤት እንድትሆን ያስቻለች ልዩ መለያ ናት። እኛም እንደ ጳጉሜን ድልድይ ሆነን ወጣቶቹ ከአስከፊው የጎዳና ተዳዳሪነት ሕይወት ተላቀው ወደ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ እናደርጋለን በሚል እሳቤ እንዲሁም የጳጉሜን ልዩ መገለጫነት እንደ መታሰቢያ ለመጠቀም በማሰብ የድርጅቱ ስያሜ ‹ጳጉሜን አምስት (፭)› እንዲሆን ተደርጓል›› በማለት ያብራራሉ።



አርቲስቶች፣ ደራሲያን፣ ስፖርተኞች፣ ጋዜጠኞችና ሌሎች ባለሙያዎች የበጎ አድራጎት የድርጅቱ የበጎ ፈቃድ አምባሳደር ሆነው ይሰራሉ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
AUTHORITY FOR CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS

የምዝገባ የምስክር ወረቀት

ጳጉሜን አምስት (፭) በጎ አድራጎት ድርጅት የተባለ አገር በቀል ድርጅት የቀድሞውን ስያሜ በመለወጥ በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት ጳጉሜን 5 ቀን 2011 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 4434 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ተሰጥቶታል።

CERTIFICATE OF REGISTRATION

This is to certify that PAEGUME AMEST (5) CHARITY ORGANIZATION changing its former name, has been registered and accorded legal personality with Registry Number 4434 on September 10, 2019 as Local Organization in accordance with the Civil Society Organizations Proclamation No. 1113/2019.

❖ New name issue date:- February 29, 2024

❖ Former name: - PAECUME AMEST (5) GEBERESENAY DIRJITE

‹‹ጳጉሜን አምስት (፭)›› የበጎ አድራጎት ድርጅት ዋና ትኩረቱ ጎዳና ላይ የሚኖሩ ወጣቶች ናቸው። እነዚህን ወጣቶች ከጎዳና ላይ በማንሳት ቤት ተከራይቶ መጠለያ፣ ምግብ፣ አልባሳት፣ የቤት ቁሳቁስና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን የማቅረብ፤ የሥነ ልቦና ስልጠና የመስጠት፣ የትምህርትና የሥራ እድሎችን የማመቻቸት አገልግሎቶችን ይሰጣል። ቀደም ሲል ድጋፍ የሚያደርገው ወጣቶቹ ባሉባቸው አካባቢዎች (በጎዳናዎች ላይ) ነበር።

‹‹ጳጉሜን አምስት (፭)›› እስካሁን ባከናወናቸው የበጎ አድራጎት ሥራዎች አማካኝነት ከ10ሺ በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻለ ማስተር ኤርሚያስ ይናገራሉ። ‹‹የመጠለያ፣ የምግብና የአልባሳት አቅርቦት፣ የትምህርት፣ የማዕድ ማጋራት፣ የሥራ እድል ፈጠራና የሥነ ልቦና ስልጠና አገልግሎቶችን ሰጥቷል። በድርጅቱ ድጋፍ የተደረገላቸው ወጣቶች በተፈጠረላቸው የሥራ እድል አማካኝነት የሙያ ክህሎታቸውን አሳድገዋል። በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም (እንደ የእምነታቸው) በጣም ጠንካራ የሆኑ ወጣቶች አሉ። በድርጅቱ ድጋፍ ለተሻለ ሕይወት የበቁ ወጣቶችን በመሸለም፣ ሌሎች የጎዳና ተዳዳሪዎችም ተስፋ እንዲኖራቸውና እንዲበረታቱ እናደርጋለን›› በማለት ያብራራሉ። ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ቤት ተከራይቶ ለ30 ልጆች ቋሚ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በቀጥታ ከድርጅቶች የምናገኘው ቋሚ ድጋፍ የለም። የድርጅቱ መርህ ‹‹የራስን ችግር በራስ አቅም መፍታት›› ነው። ዓላማውና መነሻው እንደሌሎች ድርጅቶች ከውጭ ተቋማት የሚገኝን ገንዘብ ለመጠቀም አይደለም። ድርጅቱ ገንዘብ የሚያገኘው በተቻለ አቅም ከመንግሥት አካላት ጋር በመቀናጀት በተለያዩ አካባቢዎች (መንገዶች ላይ) በመዘዋወር ስለድርጅቱ ገለፃ በማድረግ ለጋሾችን ድጋፍ እንዲያደርጉ በመጠየቅ፣ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ አካላት በሚያደርጉት ድጋፍ እንዲሁም ከአባላት በሚሰበሰብ መዋጮ ነው።

‹‹ትያትር ቤቶች የአንድ ቀን ገቢያቸውን እንዲሰጡን በማድረግ ገቢ እናገኛለን። እኔ ተማሪዎችን የማሰለጥንበት ስፖርት ቤት ማስ ስፖርት አዘጋጅቶ ቲሸርት ይሸጣል፤ ከሽያጩ የሚገኘው ገቢ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ገቢ ይሆናል። በአጠቃላይ ገንዘብ የምናገኘው በሀገር ውስጥ ከምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ነው። አርቲስቶች፣ ደራሲያን፣ ስፖርተኞች፣ ጋዜጠኞችና ሌሎች ባለሙያዎች የበጎ አድራጎት የድርጅቱ የበጎ ፈቃድ አምባሳደር ሆነው ይሰራሉ›› በማለት ስለድርጅቱ የገንዘብ ምንጭ ያስረዳሉ።

‹‹ጳጉሜን አምስት (፭)›› የበጎ አድራጎት ድርጅት ሥራዎቹን ሲያከናውን ስለሚያጋጥሙት ችግሮችም ማስተር ኤርሚያስ ያስረዳሉ። ‹‹መንግሥት ለበጎ አድራጎት ሥራዎች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችንና አሠራሮችን ቢዘረጋም፣ በየደረጃው ያሉ አንዳንድ የመንግሥት አካላት ለሥራዎቹ ተባባሪ የማይሆኑባቸው ጊዜያት አሉ። ለአብነት ያህል ድጋፍ የማሰባሰብ ሥራዎችን በምናከናውንበት ወቅት አንዳንዶቹ ተቋማትና የሥራ ኃላፊዎች ፈቃድ ይሰጣሉ፤ አንዳንዶቹ ግን ሥራውን እንዳናከናውን ይከለክላሉ። ድጋፍ የሚደረግላቸው ግለሰቦች የግል ፀባይም ሌላው ችግር ነው። ግለሰቦቹ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ወደ ጎዳና ወጥተው አስከፊ ሕይወት ያሳለፉ በመሆናቸው አስተሳሰባቸውን ለመቀየር ጊዜ ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ ብዙ ገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት አውጥተን ወደ መደበኛ ሕይወት ለመመለስ ብዙ የደከምንባቸው ግለሰቦች ተመልሰው ወደ ጎዳና ሊወጡ ይችላሉ›› ይላሉ። የመጠለያ ችግር ሌላው ተግዳሮት እንደሆነም ይናገራሉ።

‹‹ጳጉሜን አምስት (፭)›› የበጎ አድራጎት ድርጅት ላከናወናቸው ምግባረ ሰናይ ተግባራት ከቦሌ ክፍለ ከተማና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እውቅናዎችንና ሽልማቶችን አግኝቷል። ‹‹ድርጅቱ የራሱ ገቢ ኖሮት ሴቶች በባልትና ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ (እንጀራ፣ ሽሮ፣ ቆሎ፣ ቅመማ ቅመም ... እንዲያዘጋጁና የገበያ እድል ተመቻችቶላቸው ምርቶቻቸውን በየቤቱ እየዞሩ እንዲያከፋፍሉ...)፣ ወንዶቹ ደግሞ በብሎኬት ማምረት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ እንዲሁም ድርጅቱ የራሱ ማዕከል ኖሮት ወጣቶቹ በማዕከሉ ውስጥ የከተማ ግብርና ሥራዎችን በመሥራት የገቢ ምንጭ እንዲያገኙ የማድረግ እቅድ አለው›› በማለት ስለድርጅቱ እቅዶች ይናገራሉ።

ማስተር ኤርሚያስ የበጎ አድራጎት ተግባራት ከዕለታዊ ርዳታ ተሻግረው በግለሰቦች ሕይወትና በማኅበረሰብ ገፅታ ላይ ዘላቂ ለውጥ እንዲያስገኙ ኅብረተሰቡ፣ የበጎ አድራት ተቋማት፣ ድጋፍ ፈላጊዎችና መንግሥት የየራሳቸው ኃላፊነቶች እንዳሉባቸው ያስገነዝባሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፣ ህብረተሰቡ በተናጠል የሚያደርገውን ድጋፍ ተቋማዊ በሆነ መልኩ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲያበረክት መበረታታት አለበት። በተናጠል የሚደረጉ ድጋፎችን በኅብረት በማድረግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች በተሻለ አቅም ተደራሽ ማድረግ ይቻላል። በተናጠል የሚደረጉ ድጋፎች ዕለታዊ/የአጭር ጊዜ ፋይዳ ቢኖራቸውም ዘላቂ መፍትሔ መሆን አይችሉም፡፡

ድጋፍ የሚደረግላቸው አካላት ደግሞ ድጋፍ አድራጊ ግለሰቦችና ተቋማት መነሻ የሚሆን ድጋፍ ካደረጉላቸውና መንገዱን ካመለከቷቸው የራሳቸውን ጥረት ጨምረው መንገዱን ተከትለው ከችግሮቻቸው ለመውጣት መጣር አለባቸው።

መንግሥት ደግሞ የማኅበረሰብን ችግሮች ለማቃለል ለሚጥሩ የበጎ አድራጎት ተቋማት ክትትል በማድረግ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል። ብዙ ግለሰቦችና ተቋማት የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ጀምረው ሲያቋርጡ ይስተዋላል። ለዚህ ችግር አንዱ ምክንያት በመንግሥት አካላት በኩል የሚታየው የድጋፍና ክትትል ማነስ ነው። ስለሆነም የበጎ አድራጎት ተግባራት ድጋፍ የሚደረግላቸውን አካላት ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት በሚያስችል መልኩ እንዲሰሩ መንግሥት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል።

**ድርጅቱ እነዚህን ወጣቶች ከጎዳና ላይ በማንሳት ቤት ተከራይቶ መጠለያ፣ ምግብ፣ አልባሳት፣ የቤት ቁሳቁስና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን የማቅረብ፤ የሥነ ልቦና ስልጠና የመስጠት፣ የትምህርትና የሥራ እድሎችን የማመቻቸት አገልግሎቶችን ይሰጣል**

# ስፖርት





# የመጀመሪያው የወርቅ ሜዳሊያ ተስፋ!

**ቦጋለ አበበ**

የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ የአትሌቲክስ ውድድሮች ትናንት ጀምረዋል። ኢትዮጵያ በውድድሩ የወርቅ ሜዳሊያ ለማስመዝገብ ትልቅ ተስፋ ካደረገችባቸው ርቀቶች አንዱና ዋነኛው የወንዶች 10ሺ ሜትር ፉክክር ዛሬ ምሽት 4:00 ይካሄዳል።

የቶኪዮ 2020 የርቀቱ አሸናፊ አትሌት ሰለሞን ባረጋ፣ ዮሚፍ ቀጀልቻና በሪሁ አረጋዊ በዚህ ፉክክር ኢትዮጵያን የሚወክሉ ወጣት አትሌቶች ሲሆኑ ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምትም ተሰጥቷቸዋል። ሦስቱ አትሌቶች ባለፉት ዓመታት በርቀቱ ኢትዮጵያን በዓለም ሻምፒዮናና ኦሊምፒክ መድረኮች ወክለው ብርቱ ተፎካካሪ በመሆን ትልቅ አቅም እንዳላቸው አሳይተዋል። እነዚህ አትሌቶች በውድድር ዓመቱ ምርጥ ብቃት ላይ ከመገኘታቸው በተጨማሪ በልምድም በስለው ነው ለዛሬው ፍልሚያ የሚቀርቡት።

ከሁለት ኦሊምፒኮች በኋላ የርቀቱን ድል ወደ ኢትዮጵያ የመለሰው ሰለሞን ባረጋ ፓሪስ ላይ ተመሳሳይ ድል ለመድገም ጠንክሮ ሲዘጋጅ የቆየ አትሌት ሲሆን ዳግም የወርቅ ሜዳሊያውን የማጥለቅ ጉጉት እንዳለው በዝግጅቱ ወቅት ተናግሯል። ሰለሞን ከቶኪዮ በኋላ በተካሄዱት ሁለት የዓለም ሻምፒዮናዎች በርቀቱ ወርቅ ማጥለቅ ባይችልም አሁን ካለበት አቋም አኳያ የዓለም ሻምፒዮናዎች ላይ የነበረውን ድክመት አርሞ ወደ ፍልሚያው ሜዳ እንደሚገባ ይጠበቃል።

ከወር በፊት በማላጋ በተካሄደው የኢትዮጵያውያን የኦሊምፒክ ማጣሪያ ውድድር ላይ ሰለሞን ዮሚፍ ቀጀልቻንና በሪሁ አረጋዊን ተከትሎ ሦስተኛ ሆኖ ነበር ያጠናቀቀው። ይሁን እንጂ በርቀቱ ኦሊምፒክ ላይ ወርቅ የማጥለቅ እንዲሁም የፉክክሩን መንፈስ የመረዳት ልምዱ ከሁሉም ተፎካካሪዎቹ የበላይ ያደርገዋል።

በኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ወንዶች ውድድር አንድ የተለመደ ባሕል አለ። ከፓቮ ኑርሚ እስከ ኤሚል ዛቶፔክ፣ ከላሲ ቪረን እስከ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ከቀነኒሳ በቀለ እስከ ሞ ፋራህ አንድ ጊዜ በርቀቱ ኦሊምፒክ ላይ ያሸነፈ አትሌት በቀጣይም ባለድል ሆነው ታይተዋል። ሰለሞን የእነዚህን የቀድሞ ከዋክብት ታሪክ ይደግማል ወይስ አዲስ ሻምፒዮን ይታያል? ብዙዎች በጉጉት የሚጠብቁት ነው።

የ24 አመቱ ኮከብ አትሌት ሰለሞን ዳግም በርቀቱ ለመንገሥ ጉጉት የሚያሳድርበት ሌላም ምክንያት አለው። በኢትዮጵያ የኦሊምፒክ የወንድ አትሌቶች ታሪክ ከአንድ በላይ የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ ታሪካዊው አበበ ቢቂላ፣ ኃይሌ ገብረሥላሴና ቀነኒሳ በቀለ ብቻ ተጠቃሽ ናቸው። ሰለሞን ከእድሜው አኳያ ሌላ የኦሊምፒክ ዕድል ቢኖረውም ዘንድሮ ሁለተኛውን የኦሊምፒክ ወርቅ አጥልቆ ከወዲሁ የእነዚህን ሕያው ከዋክብት ታሪክ መጋራት ይፈልጋል።

ሌላኛው ኢትዮጵያዊ የርቀቱ ኮከብ ዮሚፍ ዘንድሮ የተለየ ድንቅ ብቃት ላይ ይገኛል። በማላጋው ማጣሪያ ቀዳሚ ከመሆኑ ባሻገር የውድድር ዓመቱን ፈጣን ሰዓት እንዲሁም የርቀቱን የምንጊዜም ስድስተኛ ፈጣን ሰዓት በ26:31.01 አስመዝግቧል። የ27 ዓመቱ ኮከብ ከስምንት ዓመት በፊት በሁለት ተከታታይ የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮናዎች የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቅ ቢችልም በኦሊምፒክና በዋናው የዓለም ሻምፒዮና ወርቅ ማሳካት አልቻለም። በነዚህ ዓመታት ግን የኦሊምፒክ ወርቅ ሲያልም ኖሯል። ይህን ሕልሙን እውን ለማድረግ ፓሪስ ትክክለኛው ጊዜ ይመስላል። በዚህ ኦሊምፒክ በ5ሺ ሜትርም የመወዳደር ዕድል የነበረው ቢሆንም በመጨረሻ ሰዓት በ10ሺ ሜትር ብቻ ለመሮጥ ተገዷል። ሙሉ ትኩረቱና ዝግጅቱም በዚሁ ርቀት ብቻ ይሆናል።

በማላጋው ማጣሪያ ሁለተኛ ሆኖ ያጠናቀቀው የ23 ዓመቱ ወጣት ኢትዮጵያዊ ኮከብ በሪሁ አረጋዊ በኦሊምፒክና የዓለም ሻምፒዮና በርቀቱ ልምድ እያካበተና እየበሰለ የመጣ አትሌት ነው። የ2023 የዓለም ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና የብር ሜዳሊያ አሸናፊም ሲሆን በቶኪዮ ኦሊምፒክም አራተኛ ሆኖ ነበር ያጠናቀቀው። ዮሚፍ የዓመቱን ፈጣን ሰዓት ባስመዘገበበት ውድድርም በጥቂት ሰከንዶች ብቻ ነው የተበለጠው። ይህ ትልቅ አቅም ያለው ወጣት ኮከብ ሁሌም ውድድሮች ከመጀመራቸው አስቀድሞ ለአሸናፊነት ከሚታጩ አትሌቶች ዝርዝር ውስጥ አይጠፋም።




**ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዓመቱ ባሳዩት ብቃት ከሌሎች ሃገራት ተፎካካሪዎች የተሻለ የአሸናፊነት ግምት ተሰጥቷቸዋል፣**

ሦስቱ ኢትዮጵያውያን እንደቡድን ተረዳድተው መሮጥ ከቻሉ አንድ የተለየ ታሪክ ሊሠሩ የሚችሉበት አቅም አላቸው። ምናልባትም 1936 ላይ የፊንላንድ አትሌቶች በርቀቱ ሁሉንም ሜዳሊያ ጠራርገው የወሰዱበትን ብቸኛ ታሪክ ሊደግሙ ይችላሉ ብለው የዓለም አትሌቲክስ ፀሐፍትም ግምታቸውን አስፍረዋል። ይህን ለማድረግም ይሁን የወርቁን ሜዳሊያ ለማጥለቅ ግን አንድ ከባድ ፈተና ይጠብቃቸዋል። ያም ያለፉት ሦስት የዓለም ሻምፒዮናዎች አሸናፊውና የርቀቱ የክብረወሰን ባለቤት ዑጋንዳዊው ጆሽዋ ቺፕቴጌ ነው።

ቺፕቴጌ በዚህ የፈረንጆች ዓመት በ10ሺ ሜትር ምንም አይነት ውድድር ላይ አልታየም። ከሁለት ወር በፊት ግን በ5ሺ ሜትር ዘጠነኛ ሆኖ ነበር ያጠናቀቀው። ወቅታዊ አቋሙ ባይታወቅም ምናልባትም ለዛሬው ፍልሚያ ድምፁን አጥፍቶ ሲዘጋጅ እንደከረመ ግን መገመት አይከብድም። ቺፕቴጌ ቶኪዮ ኦሊምፒክ ላይ በርቀቱ በሰለሞን ተቀድሞ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀበትን ቁጭት በ5ሺ ሜትር እዚያው ቶኪዮ ላይ መወጣት ቢችልም የ10ሺ ሜትሩን ክብር ማሳካት ካለበት ከፓሪስ የበለጠ ጥሩ አጋጣሚ የለውም። ለዚህም ነው ለኢትዮጵያውያኑ ከዋክብት ትልቅ ፈተና ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው።

የኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ስጋት የሚሆነው ቺፕቴጌ ብቻ አይደለም። የምንጊዜም ኃያል ተፎካካሪ የሆኑት ኬንያውያንም ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም። ዳንኤል ማቴኮና የዓለም የ5 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር የነሐስ ሜዳሊያ አሸናፊው ኒኮላስ ኪፕኮሪር ፈጣን ሰዓት ያላቸው ኬንያውያን ናቸው። በዚህ የፈረንጆች ዓመት በራስ አል ካይማህ ግማሽ ማራቶን ያሸነፈው ማቴኮ ከወር በፊት ዩጂን በኬንያውያን የኦሊምፒክ ማጣሪያ የራሱን ፈጣን ሰዓት በ26:50.81 አስመዝግቦ አሸንፏል። ኪፕኮሪር ደግሞ በሰከንዶች ልዩነት ሁለተኛ ሆኖ ያጠናቀቀ ሲሆን በቶኪዮ ኦሊምፒክ በ5ሺ ሜትር አራተኛ ሆኖ ነበር የፈፀመው።